## የአዋጭ ብራንድ አምባሳደሯ አርቲስት መቅደስ ፀጋዬ

**በ አቶ ጌታሁን ታደሰ**

በስምጥ ሸለቆዋ እምብርት አዳማ-ናዝሬት እድገቷን አደረገች፤ የመገኘት ምክንያት ከሆኗት ከእናቷ ከወ/ሮ ሮማን ለማ እና ከአባቷ አቶ ፀጋዬ ሀብቴ የተወለደች፤ 1 ሜትር ከ72 ሴንቲሜትር ቁመት የተቸራት፤ ቁመቷን ከ70 ኪ.ግ ክብደቷ ጋር ያጣጣመች፤ በፊልም ኢንደስትሪው የ14 ዓመታት የስራ ልምድን ያካበተች፤ ሙያዋን በዕውቀት ለማከናወንና የቢዝነስ ነክ አድማሷን ለማስፋት ከማሃሪሽ ኢንተርናሽናል ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን የማስተርስ ዲግሪ፤ በአሜሪካን ሀገር ከሚገኘው ባርክሌይ ኮሌጅ ደግሞ በኢንተርናሽናል ቢዝነስ የባችለር ዲግሪ መያዟ መልካም ተፅዕኖ ፈጣሪነቷን ከፍ እንዲል ያደረጋት ባለ-ታሪክ! በኢቢኤስ ቴሌቭዥን ለአምስት ተከታታይ ዓመታት የተመልካችን ቀልብ ገዝቶ በነበረው "ሞጋቾች" በተሰኘው ተከታታይ የቴሌቭዥን ድራማ ላይ የዶ/ር ኮከብን ገፀ-ባህሪ ተላብሳ ከመተወን ባለፈ ዳይሬክተር፣ መሪ ተዋናይና ፕሮዲዩሰር በመሆን አድናቆትን ያተረፈች፤ የሌሊት ጧፍ በተሰኘው ኢቢኤስ ላይ በተከታታይ ሲተላለፍ በነበረው የቴሌቭዥን ድራማ ላይ መሪ ተዋናይና ፕሮዲዩሰር፤ በዋልታ ቴሌቭዥን ሲተላለፍ በነበረው "ግማሽ ጨረቃ" በተሰኘው ተከታታይ የቴሌቭዥን ድራማ ላይ ዳይሬክተር፣ መሪ ተዋናይና ፕሮዲዩሰር በመሆን ሰርታለች። በFeaure Films ደግሞ ትስስር፣ የአዳም ገመና፣ ዘራፍ እና የከረመ የተሰኙትን ስራዎች በራሷ የፕሮዳክሽን ኩባንያ አማካኝነት የፊልሙ ፀሐፊ፣ መሪ ተዋናይና ፕሮዲዩሰር በመሆን ለህዝብ አድርሳለች።

ስሟ ለብዙዎቻችን ጆሮ አዲስ አይደለም አርቲስት መቅደስ ፀጋዬ ሀብቴ ትባላለች። አርቲስት መቅደስ በፕሮዳክሽኑ ዘርፍ ያላትን ዕውቀት ለማሸጋገር መቅዲ ፕሮዳክሽን የተሰኘ የራሷን ድርጅት በማቋቋም ድርጅቱን በዋና ስራ አስኪያጅነት እያስተዳደረች ትገኛለች።

አርቲስት መቅደስ ፀጋዬ የአዋጭ የኅብረት ሥራ ማኅበርን ሳይጨምር ከ14 በላይ ለሚሆኑ ድርጅቶች ብራንድ አምባሳደር የነበረች ሲሆን ከነዚህም መካከለ ለኢትዮጵያ ልማት ባንክ፣ ለአባይ ባንክ፣ ለታደሰ ፍላቴ፣ ለቡና ኢንሹራንስ፣ ለአሜሪካን ኮሌጅ ኦፍ ቴክኖሎጂ፣ ለአቦል ቲቪ (ዲኤስ ቲቪ) ፣ ለማሃርሽ ኢንተርናሽናል ዩኒቨርሲቲ፣ ለሪያሊቲ ሪል እስቴት፣ ለቡልቴክስ-ሱና፣እንዲሁም በበጎ ፍቃደኝነት አምባሳደርነት ደግሞ ለሀበሻ አረጋውን ማዕከል ፣ ለጆይ ኦቲዝም ማዕከል ፣ ለመቄዶንያ ፣ ለሜሪ ጆይ እና ስለ-እናት የበጎ አድራጎት ማዕከል ተጠቃሽ ናቸው።

የአርቲስቷ የስኬት ጉዞ በብዙ ስጦታዎች፣ ችሎታዎችና ትጋቶች የታጀቡ ናቸው። **ሁለንተናዊ ሴት ናት፤ ታታሪ!** በሀገር ውስጥ የሞዴሊንግ (Modeling) ውድድሮች አርዓያ መሆኗን ያስመሰከረች፤ በአሜሪካን ሀገር፤ በኒው ዮርክ ከተማ በሴፕቴምበር ፋሽን ዊክ ኢንተርናሽናል ሞዴል እስከመሆን ብቃቷን ያሳየች ብርቱ ሴት ናት ስመ ጥሯ፤ ስመ ጥሩዋ አርቲስት መቅደስ ፀጋዬ ሀብቴ።

አርቲስቷ በተለያዩ የማስታወቂያ ስራዎች ላይ ተሳትፋለች ለአብነት ያህል የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበርን፣ ሱና አድቨርታይዚንግን፣ አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካን፣ ሰንሲልክ የውበት

መጠበቂያ ምርትን፣ ኪዩት ቤቢን፣ አፍሮዲጡን፣ ኢንተርኮንቲነንታል ሆቴልን፣ ሚራክል ሳሙናን (የኢስት አፍሪካ ታይግር ብራንድ) እና ሪያሊቲ ሪል እስቴትን በማስተዋወቅ በማስታወቂያ ኢንደስትሪው ዘርፍ የራሷን አሻራ አሳርፋለች።

በሙያዋ ሀገርንና ወገንን ከማገልገል ባለፈ በማህበራዊ ተሳትፎዋ ደግሞ ጉልህ አስተዋፅኦ በማድረግ የሚጠበቅባትን ድርሻ በሚገባ እየተወጣች የምትገኝ የህዝብ በረከት ናት። በዚህም የአዲስ አበባ ከተማ የሰላም ካውንስል ምክትል ፕሬዚደንት ሆና በማገልገል፣ የአፍሪካ ሴት መሪዎች መረብ ምክትል ፕሬዚደንት፣ የኩላሊት ታማሚያን የበጎ አድራጎት ድርጅት የዕውቅና ሰርተፊኬት ያገኘች፣ ከእንረዳዳ የአረጋውያን ማኅበር የዕውቅና ሰርተፊኬት ያገኘች፣ ከሜሪ ጆይ የዕውቅና ሰርተፊኬት ያገኘች፣ የዝም አልልም የማኅበዊ ንቅናቄ መስራች፣ በክቡር ዶ/ር አቢይ አህመድ የሚመራውን የሸገርን እናስውብ ፕሮጀክት ተሳታፊ፣ ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊንየም ሜዲካል ኮሌጅ የስነ-ፆታ ክለብ የዕውቅና ሰርተፊኬት ያገኘች ታላቅ ሴት ናት።

በጠንካራ ስራና ትጋት የተቃኘ ማንነት ሽልማት ያጎናፅፋል። አርቲስት መቅደስ ፀጋዬም የዚሁ አባባል ተቋዳሽ በመሆን የበርካታ ሽልማት ባለቤት መሆን የቻለች ጠንካራ ሴት ናት። የጉማ አዋርድ ምርጥ እጩ ተዋናይ በመሆን በ2011 ዓ.ም ተሸላሚ የሆነች፣ በተከታታይ የቴሌቭዥን ድራማ ምርጥ የለዛ አዋርድ እጩ ተዋናይ የሆንች፣ ከቀድሞ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ም/ጠ/ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የምስጋና ሰርተፊኬት ሽልማት፣ ከኢቢኤስ ቴሌቭዥን ሰርተፊኬት ሽልማት እና ከኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚደንት ሳህለወርቅ ዘውዴ እጅ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የሰርተፊኬት ሽልማት የተበረከቱላት ሲሆን በቅርቡ እንኳን አርቲስት መቅደስ ፀጋዬ ተፈጥሮና የግል ትጋቷ ባጎናፀፏት የማሳመን ልዩ ችሎታ የግሪክ፣ ሳይፕረስና ሰርቢያ የህክምና



ቡድኖች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በጤና እና ቱሪዝም ላይ እንዲሰሩ በማድረግ እንዲሁም በሀገሮች መካከል የልማት ግንኙነቶች እንዲፈጠሩ በማድረግ ረገድ ላበረከተችው አስተዋፅኦ ከግሎባል ዶክተርስ ሄፖክራቲክ ኢንስቲትዩትና ከግሪክ የጤና ቱሪዝም ካውንስል የዕውቅና ሽልማት የተበረከተላት እጅግ ጠንካራና ስኬታማ ሴት ናት።

አዋጭ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃላፊነቱ የተወሰነ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበር ይህችን ኅበዝ፣ ትጉህ፣ ታታሪ፣ ተፅእኖ ፈጣሪና ሰርቶ-ከበር ዜጋ የኅብረት ሥራ ማኅበራችን የብራንድ አምባሳደር አድርጎ ሾሟታል። ክብርት አምባሳደር አርቲስት መቅደስ ፀጋዬ ባላት የመሰማት አቅምና ልዩ የማሳመን ችሎታ የኅብረት ሥራ ማኅበራችንን ወደ ተሻለ ደረጃ እንደምታሸጋግር ባለሙሉ ተስፋ ነኝ።

## ቁጠባ በአዋጭ

**በአቶ ይርጋለም**

የሰው ልጅ ፍላጎት የተለያየ ከመሆኑ ባሻገር በየቀኑ ከዕለት ወደ ዕለት ሊለዋወጥ፣ ሊጨምርና ሊሻሻል ይችላል። በእያንዳንዱ ደቂቃ አዕምሮ ያወጣል ያወርዳል ያመዛዝናል ይወስናል በዛው ቅፅበት የነገን ተግብሮ ያሳያል ያየውን ራዕይ በተጨባጭ የማምጣት ክህሎት እንደየ ግልሰቡ ደሞ ይለያያል ። ሁሉም እንደየ እምነቱ በፀሎት ፈጣሪውን ይጠይቃል በተጓዳኝ እንደየ ቅርበቱ አጠገቡ ከሚገኙ ከቤተሰቡ፤ ከጓደኞቹ ከጎረቤት ከስራ ባልደርቦቹ አልፎ ተርፎ ከአማካሪዎቹ ጋር ይመክራል፤ ይማከራል፤ ይወያያል፤ የተሻለ የሚለውን ይይዛል፤ የማይሆነውን ይተዋል፤ ጊዜ ወስዶ ራሱ ያስባል። ታዲያ ድህነትን ለመዋጋት የሚታገል ሀሳብ ራዕይ ይሰንቃል፤ ራዕይ ያለው ሰው ነገን ያስባል። በዚህም አንድ ብሎ የሚጀምረው ዛሬ ነው ከዛሬም አሁን ነው። ይህ ከዛሬ 17 ዓመት በፊት ወደ ኋላ ተጉዘን ስናስበው የተፈጠረው ይህ ነበር። ቁጭ ብሎ በሀሳብ ከመኳተን የመለወጫ መንገዶችን መምረጥ ፤ ድህነትን እምቢ ማለት፤ ሊያግዙን የሚችሉ ሰዎችን ማማከር፤ ሊረዱን የሚችሉ ልምድና ተሞክሮዎችን ማጤንና አቅጣጫን መቀየስ ወሳኝ ምዕራፍ ነው። ትክክለኛ ሀሳብ ላይ መምጣቱ ብቻ ባለ ድል አያደርግምና ለአዲስ ለውጥ ቆራጥነት እጅግ አስፈላጊ ነገር በመሆኑ የአዋጭ መስራች የሆኑት አቶ ዘሪሁን ሽለመ ለሁሉም አዋጭ የሆነ ሀሳብ በማፍለቅ ቆጥበን እንለወጥ ፣ መቆጠብ መሰልጠን ነውና ሲሉ ታላቅ ራዕይ አንግበው ተነሱ። ዕለት ከዕለት ሀብታም ደሃ ዘር ቀለም ሃይማኖት ሳይለይ በጋራ ድህነትን ለማሸነፍ ቁጠባን ለማሰባሰብ አዋጭ ተጀመረ። ድሃ እናቶች ከመቀነታቸው በጥቂት በጥቂቱ ይቆጥቡ ጀመር። በአንድ ወቅት መስራቹ አቶ ዘሪሁን በአንድ መገናኛ ብዙሃን ሲጠየቁ እንደተናገሩት ገቢ የሌላቸው እናቶች "ሽሮ በርበሬ ያዋጡ ነበር" ሲሉ ተደምጠዋል። ሁሉም ሲሳተፍ በማህበሩ ለውጥ መጣ፤ የግለሰቦች ሕይወት እየተለወጠ መጣ። በማህበሩም የተጠቀሙ ዜጎች ሲጠየቁ ይህ ዓይነት አሰራር በእውነት አዋጭ ነው ብለው የምስክርነት ቃል ሲሰጡ ተሰሙ፤ ከዛ ቀን ጀምሮ ሁሉም አባል በመስማማት አዋጭ በሚል የማህበር መጠሪያ ስም ተሰየመ ስሙም ከፍ በሚል ድምጽ በተግባሩም ተመሰከረ። ሲመሰረት የነበረው ራዕይ ቀጠለ መመሪያ ደንብ ወጣ አባላት ሲለወጡ ታዩ ምስክርነት ሰጡ ዕድገት ያስመዘገበ ማህበር ላይ መሳተፍ የሚፈልጉ ዜጎች በየአቅጣጫው ጥያቄ አቀርቡ ወደዚህ የዕድገት

ጉዞ ተቀላቀሉ። በዚህም መንገድ ነው እንግዲህ አዋጭ ወደ ዕድገት ማማ የወጣው። ለስኬቱ ዋናው ምስጢር በህብረትና በታማኝነት መስራቱ ነው። ያለምንም ጥቅም በወቅቱ የነበሩት ባለራዕይ ለነበራቸው ራዕይ በቁርጠኝነት መሰዋትነት ከፍለዋል። ሙሉ ትኩረት ሰጥተው የተሰበሰበን ገንዘብ ውጠታማ በሆነ መንገድ በማስተዳደር ህብረት ስራ ማህበሩን ስኬታማ ማድረግ ተችሏል። በዚህ የስኬት ጎዳና ዕድሜ፣ ትምህርት፣ ብሔርና ሐይማኖት ሳይለዩ አካታች በሆነ አሰራር የህብረት ስራ ማህበሩን ዓላማ እውን ማድረግ ተቻለ። አዋጭ አሸናፊነትን በማሳየት በሁሉም ለሁሉም የሚል መርህ የተሟላ መሆኑን በአደራጅ የመንግስት መስሪያ ቤት ኃላፊዎች ተፈትሾ እንከን አልባ ሆኖ መገኘቱ የዋንጫ ተሸላሚ አድርጎታል። በዚህም አንቱ የተባሉ አርቲስቶች፣ አትሌቶች፣ ዶክትሮች፣ ፕሮፌሰሮችና የመንግስት ተሿሚ ባለስልጣናት ጭምር የማህበሩ አባል በመሆን አጋርነታቸውን አሳይተዋል፤ ተጠቃሚም ሆነዋል። አዋጭ “መቆጠብ መሰልጠን ነው ለለውጥ እንቆጥብ” በሚል መሪ ቃል ማህበረሰብን ተሳታፊ እያደረገ ነው። ከአነስተኛ ገቢ ካላቸው ግለሰቦች ጀምሮ በዚህ መሪ ቃል በመነሳሳት መንገድ ላይ ሱቅ በደረቴ እየሰሩ ከሚተዳደሩ ጀምሮ የመኪና እና የቤት ባለቤት የሆኑት አባላት አዋጭን ወደ ከፍታ ለመውሰድ ባለው የስኬት ጉዞ ላይ ባለድርሻ ናቸው። አዋጭ በተለያዩ መንገዶች የቁጠባን ባህል እያስተማረ ይገኛል። ከላይ እንዳየነው ከቤትና ከስራ ቦታ የተጀመረ ማህበር አባላትን ብቻ ሳይሆን የአባላት ልጆችንም በዚህ አዋጭ መንገድ ላይ እያሳተፈ የቁጠባን ባህል እያሰረፀ ይገኛል።

በጥቂት ሰዎች የተጀመረን ማህበር ከፍ በማድረግ ተረካቢ ትውልድን በማፍራት ወደ ሀገር አቀፍ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ተደራሽም ሆኗል። በዚህም መንገድ ከአርባ አንድ (41) አባላት ጅማሮ ወደ 132 ሺህ በላይ የሚቆጠሩ አባላትን ማድረስ ችሏል። አባላት ቁጥራቸው በዚህ መልኩ ከፍ በማለቱ የሚቆጥቡት ቁጠባም በየጊዜው እየጨመረ ይገኛል። ጅመሩ ብር 15,236.97 (አስራ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ስድስት ብር ከዘጠና ሰባት ሳንቲም) የነበረው አዋጭ ዛሬ ላይ ከ8.5 ቢሊየን ብር በላይ የፈረጠመ ካፒታል አለው።

አዋጭ ቤተሰባዊነቱ ያመዘነ፤ የግንኙነት ትስስሩን ያጠነከረ፤ የኅብረት ሥራ ማኅበርን ህግና መርህን የሚከተል ተቋም ነው። ይኸውም አባላት እርስ በእርሳቸው እንዲረዳዱና እንዲጠቃቀሙ ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ነው። አንድ አባል ሲቆጥብ ራሱን ጠቅሞ ለሌላው ይቆጥባል። አባላት በቁጠባ መሳተፋቸው የራሳቸውንና የማህበሩን አባላት ኢኮኖሚያዊ ችግር ከመቅረፋቸው ባሻገር ሀገርንና ወገንን የሚጠቅም ታላቅ ተግባር ነው።

የአባላት ምስክርነት አዋጭን በንቃትና በትጋት እንዲሰራ በአመራሩ ላይ ከፍተኛ ኃላፊነት እየጣለ ይገኛል። ለዚህም ባልፉት ሶስትና አራት ዓመታት የታዩት ለውጦች ምስክሮች ናቸው። አዋጭ ከሀገር አልፎ ራሱን በአህጉር ደረጃ በማሳደግ የአፍሪካ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበር ኮንፌዴሬሽን(ACCOSCA) ተባባሪ በአባልነት የተመዘገበ፤ እንዲሁም የአይሲኤ ICA (International Cooperative Allience) አባል የሆነ አንጋፋ የኅብረት ሥራ ማኅበር ነው። አሁን እየሄደበት ባለው የድል ጎዳና አዋጭ በ2030 ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የገንዘብ ቁጠባና

ብድር ህብረት ስራ ማህበር ሆኖ መታየት የሚችልበት ደረጃ ላይ ለመድረሱ ቅንጣት ጥርጥር አይገባውም። ይህ ሁሉ ስኬት የመጣው እያደገ በመጣ ጠንካራና የማይለወጥ የቁጠባ ባህል በአባላት ውስጥ መሰረፁ ነው።

በመጨረሻም አዋጭ መቆጠብ መሰልጠን ነው ለለውጥ እንቆጥብ ብሎ መሪ ቃል ሲያደርግ ለነገ ዛሬ እንስራ፣ በዕቅድ እንኑር የአኗኗር ዘዬን እናሻሽል፣ ለራሳችን፣ ለቤተሰብ፣ ለሀገር ለውጥና ዕድገት በአዋጭ ያሉ አባላት የሕይወት ስኬት በማምጣት አርዓያ ስለሆኑ አባላት በዕቅድ በመመራት ነገን በማሰብ የጋራ ጠላታችን የሆነውን ድህነት በመታገል ለነገይቱ ኢትዮጵያ መሰረት እንጣል። በአዋጭ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበር ቁጠባ ያልጀመራችሁ ዓላማና ራዕያችንን ከግብ ማድረሳችን ለእድገት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተን በታማኝነት እየሰራን በመሆናችን ስኬታማ በሆነው ማህበር አባል ይሁኑ፤ ይቆጥቡ፤ ቁጠባ በዕቅድ መኖርን ፤ የሕይወት ስኬትን፤ የአእምሮ ነፃነትን፤ በራስ መተማመንን ያመጣል፤ የምንለውጥበትን አቅም ይፈጥርልናልና በአዋጭ እንቆጥብ።

## የአዋጭ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃላ/የተ/መሰ/ ህብረት ሥራ ማህበር አሁናዊ ሁኔታ

**በአቶ ተስፋዬ ረጋሳ**

አዋጭ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃላ/የተ ህብረት ሥራ ማህበር ላለፉት 17 ዓመታት አባላቱን በቅንነት በማገልግል ላይ ያለ ተቋም ሲሆን በየዓመቱ እድገት እያሳየ እዚህ የደረሰ ድርጅት ነው። በመሆኑም አዋጭ ከየት ተነስቶ የት እንደደረሰ ከዚህ እንደሚከተለው በአጭሩ እንቃኛለን።

### ምስረታ

አዋጭ በ33 ሴቶች እና በ 8 ወንዶች በድምሩ በ 41 ሰዎች እና በ15,236 ብር ካፒታል በአዲስ አበባ ከተማ አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 መጋቢት/ 1999 ዓ.ም የተመሠረተ ተቋም ነው።

### ራዕይ እና ተልዕኮ

### ራዕይ

በ 2030 ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበር ሆኖ ማየት ነው።

### ተልዕኮ

አባላትን በማስተባበር ተገቢውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም በፍላጎት ላይ የተመሠረተ በሀገራችን የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ላይ አስተዋጽዖ በማበርከት ለአባላት የተሻለ የቁጠባ፣ የብድር እና ሌሎች የፋይናንስ አቅርቦት እንዲያገኙ በማድረግ የኑሮ ደረጃቸውን ማሻሻል።

### የህብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ ክልል

አዋጭ በአጠቃላይ በአገሪቱ ላይ ያሉትን የህብረተሰብ ክፍሎች በቅርብ ተደራሽ ሆኖ ለማገልገል በአዲስ አበባ 16፣ በኦሮሚያ ክልል 9፣ በአማራ ክልል ደ/ብርሃን 1፣ በደቡብ ምዕራብ ሚዛን አማን 1፣ በሲዳማ ሃዋሳ 2፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሆሳዕና 1 አና በደቡብ ህዝቦች አርባ ምንጭ1 በድምሩ 31 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከፍቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።

## የሚሰጡ አገልግሎቶች

በህብረት ሥራ ማህበሩ የቁጠባ፣ የብድር፣ የሥልጠናና ማማከር እንዲሁም የአነስተኛ የብድር መድን ሽፋን አገልግሎቶች ይሰጣሉ፡፡

በህብረት ሥራ ማህበሩ ሰባት ዓይነት ቁጠባዎች እየተሰጡ ያሉ ሲሆን እነርሱም፡- መደበኛ፣ የፍላጎት፣ የልጆች፣ የአነስተኛ ንግድ፣ የንግድ መኪና፣ የቤት አውቶሞቢል እና የመኖሪያ ቤት ቁጠባ ናቸው፡፡ የብድር ዓይነቶች ደግሞ የመደበኛ፣ የአነስተኛ ንግድ፣ የንግድ ሥራ ተሽከርካሪ፣ የቤት አውቶሞቢል እና የመኖሪያ ቤት ብድር ናቸው፡፡

## እስከ ታህሳስ 30/2016 ዓም ድረስ ህብረት ሥራ ማህበሩ ያለበትን ደረጃ የሚያሳዩ ዋና ዋና ሥራዎች መረጃ

የአባላት ዕድገትን አስመልክቶ 85,216 ወንድ እና 51,975 ሴት በድምሩ 137,191 አባላት በአዋጪ እየቆጠቡ ያሉ ሲሆን የቁጠባ መጠኑም 7.3

ቢሊየን ብር ደርሷል፡፡ ከብድር ስርጭት ጋር ተያይዞ እስካሁን 11.8 ቢሊየን ብር ለ 34,395 አባላት የተሰራጨ ሲሆን፣ 1.7 ቢሊየን ብር የካፒታል መጠን እንዲሁም 9.4 ቢሊየን ብር የሃብት መጠን በህብረት ሥራ ማህበሩ ይገኛል፡፡

## ትምህርት እና ሥልጠና

ትምህርት እና ሥልጠና አዋጭ የገ/ቁ/ብድር ህብረት ሥራ ማህበር ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች ውስጥ አንዱ እንደመሆኑ መጠን በዕቅድ ተይዞ በተከታታይነት በየዓመቱ ለአባላት እየተሰጠ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በ2016 በጀት ዓመት በስድስት ወራት ውስጥ ለ 10,021 አባላት በተለያየ የሥልጠና ርዕስ ሥልጠና በመስጠት እና ግንዛቤ በመፍጠር በህብረት ሥራ ማህበራቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡

## በአገር አቀፍ ደረጃ ካሉ ገንንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበራት በዋና ዋና አገልግሎቶች አዋጭ ያለው ድርሻ (የ2015 በጀት አመት ንጽጽር)

ከኢትዮጵያ ህብረት ሥራ ኮሚሽን የ 2015 ዓ.ም የተወሰደ መረጃ መሠረት በአገራችን ኢትዮጵያ አጠቃላይ 23,916 የገ/ቁ/ብድር ህብረት ሥራ ማህበራት ይገኛሉ፡፡ የነኚህ ህብረት ሥራ ማህበራት የቁጠባ መጠን በብር 38.7 ቢሊየን፣ የብድር ስርጭት 19.23 ቢሊየን ብር እንዲሁም ብር 11.9 ቢሊየን የካፒታል መጠን ይዘው ይገኛሉ፡፡ አዋጭ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበር ከተጠቀሱት የብር መጠኖች በቁጠባ 14 በመቶ፣ በብድር 46 በመቶ እንዲሁም በካፒታል መጠን 14 በመቶ ድርሻ ይይዛል፡፡

## የተፈጠረ የሥራ ዕድል

በአዋጭ የገ/ቁ/ብድር ህብረት ሥራ ማህበር 152 ወንድ እና 182 ሴት በድምሩ ለ 334 የቅጥር ሠራተኞች የሥራ እድል የፈጠረ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 54 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው፡፡ እንዲሁም አባላት በተመቻቸላቸው ብድር ከ 42,043 በላይ ለሚሆኑ ሰዎች የሥራ ዕድል የፈጠሩ ሲሆን ከ 100,059 በላይ የሚሆኑ የአባላት ቤተሰቦች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

## የማህበራዊ አገልግሎት መወጣትን አስመልክቶ

አዋጭ የገ/ቁ/ብድር ህብረት ሥራ ማህበር የማህበራዊ አገልግሎት ግዴታውን ለመወጣት የአዋጭ ፋውንዴሽን አቋቁሞ በስፋት በመስራት ላይ የሚገኝ ሲሆን በዚህም አዋጭ ከፋውንዴሽን ምስረታው በፊት በኦሮሚያ ክልል በጫንጮ ከተማ ሲረዳቸው የነበሩትን 200 ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ አስቀጥሎ በመርዳት ላይ ይገኛል፡፡ በአሁን ሰዓት በፋውንዴሽኑ በኩል አቅመ ደካሞችን ከመርዳት ጋር ተያይዞ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ፡፡

## ቴክኖሎጂ አጠቃቀም

ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ አዋጭ በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ በኮር ባንኪንግ ሲስተም አገልግሎት መስጠት የጀመረ ህብረት ሥራ ማህበር ሲሆን ከ 13 ባንኮች ጋር በትስስር እየሰራ የሚገኝ ተቋም ነው፡፡ በቀጣይ ከሌሎች ባንኮች ጋር የሚሰራ ሲሆን በአሁን ሰዓት ከአራት ባንኮች ጋር የሞባይል ባንኪንግ አገልግሎት ተጀምሯል፡፡


## ዓለም አቀፍ ተሳትፎ

አዋጭ የገ/ቁ/ብድር ህብረት ሥራ ማህበር ራዕዩን ለማሳካት ያግዘው ዘንድ በኢትዮጵያ ከሚገኙ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበራት የመጀመሪያው የዓለም ህብረት ሥራ ህብረት (International Cooperative Alliance/ICA/) ሙሉ አባል እንዲሁም የአፍሪካ የገ/ቁ/ብድር ህብረት ሥራ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን (The African Confederation of Co-operative Savings and Credit Association /ACCOSCA/) ተባባሪ አባል በመሆን እውቅና አግኝቷል፡፡


## በአዋጭ ከ 2014 – 2019 ዓ.ም የአምስት ዓመት ስትራተጂክ ዕቅድ በዋና ሥራዎች የተቀመጡ ቁልፍ ግቦች

አዋጭ በአምስት ዓመት ውስጥ የአባላት ቁጥርን 723,564፣ የቁጠባ መጠንን ብር 20.5 ቢሊየን፣ ቅርንጫፍ ቢሮዎችን 200፣ የቅጥር ሠራተኞችን ቁጥር 950፣ የብድር ሥርጭት መጠንን ብር 21.35 ቢሊየን ለማድረስ በትጋት እየሠራ ያለ ህብረት ሥራ ማህበር ነው፡፡






## የአዋጭ የኮርባንኪንግ አጠቃቀም ምኞት፣ ተግዳሮቶችና የአባላት ፍላጎት ማሚያ ጉዞዎች

**በአቶ ሰለሞን ወሌ**

በርካታ የሲስተም ልማት ባለሙያዎች እንደሚያምኑት ባንኮችን ጨምሮ ሌሎች የፋይናንስ ድርጅቶች የሲስተም ማበልፀግ ፈጠራ የሚመሰረተው ለሦስት ዋና ዋና ጉዳዮች ነው። እነዚህም ለደንበኞች የአገልግሎት አሰጣጥ እርካታ፣ /Customer satisfaction/ ደንበኞችን በአሠራር ብልጫ አማሎ ለመሳብ፣ /customer attraction/ እና ደንበኞች እርካታቸውን እንደጠበቁ ቆይታቸውን ለማራዘም /customer retention/ ሲባል ነው። ይህም ማለት ሲስተምን ለማልማት የሚያስፈልገው ግብዓት የደንበኞችነን ፍላጎት መሠረት ማድረግ ሲቻል ነው። ከዚህ መሠረተ-ሀሳብ ውጭ የሚነሳ የሲስተም ልማት ሁሉ መነሻም ዕድገትም የለውም። ለዚህም ዋናው ምክንያት ለመነሻ መሠረት እንደሚያስፈልገው ሁሉ ለማደግና ለመሻሻል ከፊቱ ሊከተለው የሚችል የደንበኞች መሠረታዊ ፍላጎት ሊኖረው ስለሚገባ ነው።

የአዋጭ ህብረት ሥራ ማህበር የሲስተም መዘርጋት መንፈስ ከዚህ ውጭ አይደለም። ውስን የአባላት ቁጥር በነበሩበት ዘመን እያንዳንዱን አባል ፈጠን ባለ ሁኔታ አገልግሎቱን ለመስጠት ብዙም ከባድ አልነበረም። በጊዜ ላይ ጊዜ እየተጨመረ በሄደ ቁጥር ከአባላት መበራከት ጋር በማኑዋል የሚሰጠው አገልግሎት አመርቂ ያለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ፍጥነትን፣ ጥራትንና አስተማማኝነትን ይዞ ለመጓዝ በቂ የቴክኖሎጂ መሠረተ-ልማት ያለመኖሩ ጉዳይ አሳሳቢ እየሆነ መጣ። በተግባር ደግሞ በየዕለቱ ከአባላት የሚፈሰው የተቀማጭና የብድር ተመላሽ ዳታ መበራከት በውስጥ የሂሣብ አሠራር ላይ ከባድ ተፅዕኖ በማሳረፍ በየአባላት ሂሣቦች ላይ ያልተወራረዱ ሂሣቦችን የመፍጠር ምልክቶች እየታዩ መጡ። በሌላ በኩል ከአዋጭ ውጭ በሚገኙ የፋይናንስ ተቋሞች ዘንድ የሚታየውን የአሠራር መሻሻል አባሉ እየተገነዘበ በመሆኑ ማህበሩም ይህን ፈለግ እንዲከተልለት ከመሻት ቀና አስተሳሰብና በቴክኖሎጂ ባልተደራጀው አሠራር መካከል መሰሳብ በመፈጠሩ በቴክኖሎጂ ለመሻሻል ቁልፍ መነሻ ለመሆን በቃ።

አዋጭ ከመነሻው ኮር ባንኪንግ ሲስተምን ለመዘርጋት ዘግይቶ ነበር ወይ የሚል ጥያቄ ቢነሳ

መልሱ እንዲያውም ቀድሞ ጀምሯል ነው የሚሆነው። በጊዜው ማህበሩ ካለው የካፒታል መጠንና ከተመሳሳይ ማህበራት አደረጃጀት አኳያ ሲታይ እጅግ ፈጥኖ ተግባራዊ አድርጎታል፤ ግን በስልታዊ ስምምነትና የመጪዎቹን ዘመናት የሲስተም አስፈላጊነት በተገነዘበ መልኩ።

እንደሚታወቀው ኮርባንኪንግን ተግባራዊ ማድረግ በርካታ ጥቅሞችን የሚያስገኝ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ፡

➢ ቅልጥፍናና ብቃትን ያሻሽላል (Improves Efficiency)፡ በዚህም ድርጅቶች አሠራራቸውን ከማኑዋል ወደ አውቶሜሽን እንዲለውጡ ያስችላቸዋል

➢ አደጋን ይቀንሳል (Reduces Risk)፡ ይህም ሂሣብ በማስታረቅ፣ የየዕለት ሥራዎችን በማሳለጥ፣ ሪፖርትን በማቀናጀት፣ የአዲትና ተዛማጅ ሥራዎች በተቀመጠው አሠራር መሠረት መተግበራቸውን ለመፈተሽና ለሌሎችም ጥቅሞች ይውላል

➢ የአባላትን የአገልግሎት ልምድ ከፍ ያደርጋል (Enhances customer experience)፡ አባላት የዘመናዊውን አሠራር ደረጃ በደረጃ እየተላመዱት በሄዱ ቁጥር ለበለጠ ጥቅም ሲሉ ድርጅታቸውን ለተሻለ አሠራር የሚገፋፉበት ሁኔታ ይፈጠራል

➢ የአሠራር ደንብና ህግጋትን ያሟላል (Increases compliance)፡ ደንብና ሕግጋት የድርጅቱን የውስጥ ደንቦችን፣ ፖሊሲዎችንና ሕጎችን ያካተቱ ናቸው። በዚህም አሠራራቸው ያለልዩነት ሕጋዊ፣ ስነምግባራዊና ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን የሚያረጋግጡበት መንገድ ነው።

አዋጭ የኮር ባንኪንግ ሲስተም አገልግሎትን ካስጀመረ በኋላ በየጊዜው አስፈላጊ ሞጁሎችን እያበለፀገ የውስጥ አሠራሩን በማቀናጀት ሂደት ላይ ይገኛል። ይህ አሠራር የመጨረሻውን የዕድገት ደረጃ አስይዞታል ባይባልም ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ብዙ የማስተካከያ ሥራዎችን አከናውኖ አሁን ካለበት ደረጃ

ደርሷል። በውስጥ አሠራር እያንዳንዱ በአባላት ምዝገባና በፋይናንስ ፍሰት በኩል ያለውን ለክትትል በሚያመች መልኩ ተዘጋጅቷል። እንደአብነት አንድ የሥራ ሃላፊ በየትኛውም ቅርንጫፍ የሚከናወነውን ዳታ በየደቂቃው፣ በየሰዓቱ ወይም በየቀኑ ባለው አክሰስ መሠረት ባለበት ሆኖ መከታተል ያስችለዋል። በቀኑ መጨረሻ ላይ ሲስተሙ የዕለቱን ሥራ አቀናጅቶ፣ ወጪና ገቢን አማክሎ የሚፈለገውን የፋይናንስና ፋይናንስ ያልሆኑ ሪፖርቶችን ያወጣል። በዚህም ማህበሩ በየዕለቱ ወቅታዊውን ዕቅድ ከተከናወነው ጋር እያነፃፀረ በመገንዘብ ያለበትን የዕድገት ደረጃ ለመለካት ያስችለዋል፡

የኮርባንኪንግ ሲስተም አንዱ ጥቅም ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ያለውን የሥራ ትስስር ማሳለጥ እንደመሆኑ መጠን ማህበሩ በዚህ በኩል እየተሳካለት መጥቷል። እዚህ ደረጃ ለመድረስ ግን ከበርካታ ንግድ ባንኮች ጋር ያለውን ሀብት ወደ አባላት ሒሣቦችና ወደ ማህበሩ የውስጥ አካውንቶች ለማዞር የነበረው አሠራር ብቻ ሳይሆን የሂሣብ ማስታረቁም ጉዳይ ከፍተኛው ችግር ሆኖ የቆየውን መመልከት ይኖርብናል። ይህን ለመቅረፍ ሲባል በባንኮችና በአዋጭ መካከል ያለውን የስቴትሜንት መላላክ በስዋፍት አማካኝነት ለማከናወን ታቅዶ ሊሳካ አልቻለም። የዚህ ዋና ችግር በባንክ በኩል የሚታየውን የትራንዛክሽን ማገናዘቢያ /transaction reference/ በማህበሩ አካውንቶች ላይ በማኑዋል በጥራት ለመገልበጥ ስለማያስችል በኮርባንኪንግ ሲስተሙ ላይ አውቶ ሪኮንስሊዬሽን ሞጁሉን ተግባራዊ ለማድረግ ሳይቻል መቅረቱ ነው።

ከዚህ በመነሳት ባንኮች ለአዋጭ ብቻውን ሜኑ ከማዘጋጀት ጀምሮ ስቴትሜንታቸውን በተፈለገው ጊዜ በቀጥታ ለማየት የሚያስችል አሠራር በመፍጠር የሂሣብ ማስታረቁን ሂደት ለመደገፍ ተሞክሯል። በተለያዩ ጊዚያት ልዩ ልዩ ሙከራዎች ቢደረጉም አሠራሩ በዲጅታል መንገድ ተደግፎ በአውቶማቲክ ትራንዛክሽን እስካልተካሄደ ድረስ የጠራ ውጤት እንደማይገኝ በመገንዘብ ለተሻለ ሥራ ጥረት ተደርጓል። ከነዚህ ሥራዎች መካከል ቀዳሚውና አመርቂ ውጤት የተገኘበት የባንኮችንና የማህበሩን የኮርባንኪንግ ሲስተሞች የጋራ ኢንተርፌስ ፈጥሮ በዲጅታል መንገድ ማስተሳሰር ነበር። ይህም የአፕሊኬሽን ፕሮግራሚንግ ኢንተርፌስ /API/ በማህበሩ ሁለት ዋና ዋና ሂሣብ አንቀሳቃሽ ባንኮች እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 2002 ጀምሮ ተግባራዊ ካደረጉት ወዲህ ሌሎቹ አስራ አንድ ባንኮች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በቅደም-ተከተል ሲስተማቸውን ከአዋጭ ሲስተም ጋር ሊያስተሳስሩ ችለዋል።

ይህም በመደረጉ የማህበሩና የአባላት ፍላጎት ተቀረፈ እንጂ ተሟላ ማለት ስለማያስችል የዲጂታል ትግበራውን ከባንክ ውጭ በአባላት እጅ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል። ይህም አባላት ባሉበት በየትኛውም የዓለም ክፍል ሆነው የአዋጭ አካውንቶች ከተከፈቱባቸው ባንኮች ውስጥ ካላቸው የግል ሂሣባቸው ገንዘብ ተቀናሽ በማድረግ ወይም የአዋጭ አባል ባይሆንም ከሌላ ሰው የግል ሂሣብ ላይ ወደ አባሉ አካውንት ለማስተላለፍ የሚገለገሉበት አሠራር ሊፈጠር ችሏል። ይህ የሞባይል ባንኪንግ አሠራር በአራት ባንኮች ላይ ከመስከረም ወር 2016 ጀምሮ ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን ሌሎች ዘጠኝ ባንኮች አሠራሩን ሊቀላቀሉ በሂደት ላይ ናቸው። አባላት ይህን ሲተገብሩ ለትራንዛክሽኑ ትክክለኛነት

ከማህበሩ ዳታቤዝ ጋር በማናበብ ማረጋገጥ ሲኖርባቸው በራሳቸው አምነውበትና ላስተላለፉት ሂሣብም ደረሰኝ በማውረድ መረጃ መያዝ ስለሚያስችላቸው አሠራሩ ወደ ጥራት የሚያሸጋግር ሆኖ ተገኝቷል።

እስከዚህ ድረስ ተመጥቶም ቢሆን የሂሣብ ማስተላለፍ ሥራ ከተሟላ የጥራት ደረጃ ላይ ተደርሷል ማለት አይደለም። ለዚህም ዋና ዋና መንስኤዎች የሚከተሉት ናቸው፡

1. አልፎ አልፎ የማህበሩ ኢንተርፌስ የማያውቃቸው ትራንዛክሽኖች በባንክ አካውንቶች ላይ ተላልፈው መገኘታቸው። ይህም የአዋጭ ኢንተርፌስ ከሌላቸው የባንክ ሂሳቦች ላይ ኢንተርፌስ ወዳላቸው ባንኮች በ Real-time Gross Settlement (RTGS) አሠራር በብሔራዊ ባንክ የሴትልሜንት አካውንት በኩል ወደ አዋጭ አካውንት የሚገባ የአባላት ገንዘብ አንዱ ነው። ይህም በመሆኑ ገንዘቡ ወደ ማህበሩ አካውንት ከገባ በኋላ የየትኛው አባል መሆኑንና በአዋጭ ያለውን የሂሣብ ቁጥር ስለማያሳውቅ ተጣርቶ በማኑዋል እስከሚሸጋገር ድረስ የቀናት ቆይታ ማድረጉ ነው። እዚህ ላይ የሚታየው የአባላት በየትኛውም ባንክ ሆነው ፈንድ የማስተላለፍ ፍላጎት መቅደሙንና ማህበሩ ይህን ቢያሳካ በዲጂታል አሠራር የበለጠ ተጠቃሚ መሆኑን ነው።

2. ምንም እንኳን አሠራሩ የዲጂታል ቢሆንም በየጊዜው የኔትወርክ መቆራረጥ ስለሚያጋጥም ችግሩ ባንኩና ማህበሩ ካላቸው የማቃለያ ዘዴ አልፎ ስለሚከሰት በየጊዜው የተወሰኑ ትራንዛክሽኖችን ወደጥንቱ አሠራር /ማኑዋል ፖስቲንግ/ የሚመልስበት ሁኔታ መፈጠሩ ነው። ይህ አሠራርም በተለይም የአባላት ቁጥር እየተበራከተ በሄደ ቁጥር በዚያው ልክ ተመሳሳይ በኔትወርክ መቋረጥ የሚመጣ ችግር ስለሚኖር በነባሩ አሠራር ማስተካከሉ የጥራት ደረጃውን እንደማያስጠብቀው ይታመናል።

ስለሆነም እንደዚህ ዓይነት ቀላል ግን በየመሀሉ እየገቡ ያልተገባ ጊዜ የሚወስዱ ሁኔታዎችን ተከታታይ ማሻሻያ በመሥራት ማስተካከል እንዳለብን ማህበሩ ያምናል። ከነዚህ ወደፊት ማህበሩ ካቀዳቸው ማሻሻያዎች ዘዴዎች መካከል አንዱና ዋነኛው አዋጭን በሀገሪቱ የዲጂታል ኢኮ-ሲስተም የሚቀላቀልበትን መንገድ መፍጠር ነው። የአዋጭ ዕድገት ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተያይዞ ነገር ግን በሀገሪቱ የፋይናንስ እንቅስቃሴ ውስጥ ተጣምሮ የሚሄድ ባለመሆኑ በመተግበር ላይ ከሚገኘው የሀገሪቱ የብሔራዊ ዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ (National Digital Payment Strategy) ጋር ማጣመር የግድ ይላል። ይህም ሊሆን የሚችልበት አንዱ መንገድ ባንኮችን፣ የፋይናንስ ድርጅቶችን እንዲሁም የክፍያ መግቢያ/መውጫ

(Payment gateway) አበልፃጊ ድርጅቶችን እንደሚያካትት የታመነ ሲሆን አዋጭ እንደአንድ አቅም ያለው ድርጀት በሂደት በዚህ ውስጥ መካተቱ አስፈላገነቱ እየጎላ መጥቷል።

ከላይ የተጠቀሰውን ተግባራዊ ለማድረግ እ.ኤ.አ ከ2011 ጀምሮ ኢትስዊች (EthSwitch) የተመሠረተ ሲሆን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አባልና የቦርድ ሰብሳቢነት በስሩ በርካታ ንግድ ባንኮች፣ ማይክሮ ፋይናንሶች፣ የክፍያ ኢንስትሩሜንት አበልፃጊዎች፣ የክፍያ መግቢያ/መውጫ አበልፃጊዎች፣ የፖስ፣ ኤቲኤምና ስዊች ኦፕሬተሮችን ባካተተ መልኩ ተቋቁሞ በስራ ላይ ይገኛል። ማህበሩም በዚህ ሲስተም ውስጥ ለመካተት እንደቅድመ-ሁኔታ

የብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የሚያስፈልግ በመሆኑ ከኢትዮጵያ ሕብረት ሥራ ኤጀንሲ ጋር በሚደረግ ውይይት መፍታቱ አንዱ መንገድ ሆኖ ሁለተኛው ኢትስዊች ራሱ አምኖበት ለአሠራር ክፍት ባደረገውና ከህብረት ሥራ ማህበራችን ጋር የመተማመን ውል ከሚፈፅም አንድ ባንክ አማካይነት ኢትስዊች አክሲዮን ማህበርን መቀላቀል ይሆናል፡፡ ይህ ተግባራዊ ከሆነ አዋጪ አባሎቹን በዲጂታል መንገድ ለማስታጠቅ ከዚህ በመለስ የሚለው ነገር ስለሌለ ከላይ እንደችግር የቀረበውን የአር-ቲ-ጂ-ኤስ (RTGS) አገልግሎት ብቻ ሳይሆን የኤቲኤምና የፖስ እንዲሁም የደቢት-ክሬዲት ካርድ ተጠቃሚ የሚሆንበት መንገድ ቅርብ ነው፡፡

## የአዋጭ የልምድ ልውውጥና የውጪ ሀገር ተሞክሮ

**በወ/ሮ ሩት ዳምጣቸው**

የኅብረት ሥራ ማህበራት ድህነትን ለመቅረፍ ወሳኝ መንገዶች መሆናቸውን እና ስለዚህም አፍሪካዊ እውቅና መስጠት በሰፊው ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የማህበረሰብን የኑሮ ደረጃ በማሻሻልና ድህነትን በመቅረፍ ረገድ አይነተኛ ሚና የሚጫወቱ ተቋማት ሲሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ትኩረትን አግኝተው የዓለም ሀገራት እየሰሩባቸው ይገኛል፡፡ በተመሳሳይ በአፍሪካ ከቅኝ ግዛት ጀምሮ አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ ኅብረት ሥራ ማህበራትን የማደራጀትና የመደገፍ ስራ እየተሰራ የሚገኝ ሲሆን ባለፉት አስርት ዓመታት በአፍሪካ የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንቅስቃሴ ጉልህ እድገት እያሳዩ ይገኛል፡፡ የቅርብ ጊዜ አኃዛዊ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከመቶ (100) አፍሪካውያን (ህጻናትን እና አረጋውያንን ጨምሮ) ቢያንስ ሰባት (7) ሰዎች የህብረት ስራ ማህበር አባላት ናቸው፡፡ በአብዛኛዎቹ ሀገራት ውስጥ ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት አጠቃላይ ቁጥር በእድገት ላይ ይገኛል፡፡ ምንም እንኳን የኅብረት ሥራ ማህበራት ንቅናቄ እድገት እያሳየ ቢሆንም የአፍሪካ ሀገራት ችግርም በተጓዳኝ መጨመሩን ቀጥሏል፡፡

በመሆኑንም ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጥያቄ ለአፍሪካ ልማት አስተዋጽኦ ያደርጉ ዘንድ የኅብረት ሥራ ማህበራትን እንዴት ማሻሻል እንደሚቻሉ ነው፡፡ ለዚህ እንደ ቀዳሚ ምላሽ ሊሆን የሚችለው የኅብረት ሥራ ማህበራቱን በማጠናከር ለአህጉሪቱ ልማት ውጤታማ አስተዋጽኦ ለማድረግ እንቅስቃሴዎችን መጀመር አንዱ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ በአህጉሪቱ ላይ ያሉትን የኅብረት ሥራ ማህበራት በማሰባሰብና የጋራ የልምድ ልውውጦችን በማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበራቱን በማስተባበር አህጉሪቱ እየገጠማት ያለውን ችግር ለመቅረፍ እና በሀገራቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር አይነተኛ ሚናን የሚጫወት ነው፡፡ ለዚህም አለም አቀፍ የኅብረት ስራ ኅብረት (ICA) ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ የሚገኝ ተቋም ሲሆን ይህ ተቋም በዓለም ዙሪያ የኅብረት ሥራ ንቅናቄን የሚወክል መንግስታዊ ያልሆነ የህብረት ሥራ ፌዴሬሽን ነው፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃ የኅብረት ስራ ማህበራትን በማስተባበር የትብብር እሴቶች እና መርሆዎች በማስጠበቅ እየሰራ የሚገኝ ሲሆን አለም አቀፍ የኅብረት ሥራ ኅብረት-አፍሪካ (አይሲኤ-አፍሪካ) በአፍሪካ የሚገኙ የአይሲኤ አባል ኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚያገለግል፣ አንድ የሚያደርግና የሚወክል፣ በአቅም ግንባታና በፖሊሲ ቅስቀሳ ለማኅበራዊና

ኢኮኖሚያዊ ጥቅማጥቅም ሲባል ኅብረት ሥራ ማህበራትን በማስተዋወቅና በማጠናከር ከአራቱ ክልላዊ ቢሮዎች አንዱ ነው።

የክልሉ ጽ/ቤት ሆኖ ላለፉት 51 ዓመታት ሲሰራ ቆይቷል። አይሲኤ-አፍሪካ ሁለት ክልላዊ ቢሮዎች የነበሩት ሲሆን - አንደኛው በ1968 በሞሺ ታንዛኒያ ለምስራቅ፣ መካከለኛው እና ደቡብ አፍሪካ (ROECSA) የተቋቋመ ሲሆን ሌላኛው በምዕራብ አፍሪካ (ROWA)። የROWA ቢሮ በመጀመሪያ በአቢጃን (ኮትዲቯር) ውስጥ ይገኝ የነበረ ሲሆን በኋላም ወደ ቡርኪና ፋሶ ተዛውሮ በአብዛኛው በግብርና ዘርፍ ለተሰማሩ አባላቱ ተልዕኮውን ለማስፈጸም ትልቅ ስራ ሰርቷል። የክልሉ አባልነት በዋናነት ግብርና ሲሆን ከአስራ አራቱ አባል ድርጅቶች አስራ አንዱ የግብርና ማህበራት ወይም ፌዴሬሽኖች ሲሆኑ ሌሎች ዘርፎች ቁጠባና ብድርን ጨምሮ፣ ጤና፣ ስልጠና እና ትምህርት ተወክለው ይገኙበታል።

እ.አ.አ. በሴፕቴምበር 2004 በዋርሶ የተካሄደው የICA ቦርድ ስብሰባ ሁለቱን የቀድሞ የICA ክልላዊ ቢሮዎች (ROWA እና ROESCA) ወደ አንድ የአይሲኤ ክልላዊ ፅህፈት ቤት ለአፍሪካ እንዲዋሀዱ ወስኗል። በዚያው ዓመት እ.አ.አ. (2004) ኦክቶበር በፕራያ/ኬፕ ቨርዴ የሁለቱን የICA ክልላዊ ቢሮዎች ውህደት ወደ አንድ ተቀበለ። የቦርዱ እና የክልል ምክር ቤትም ውሳኔ በመስጠት፤ በኬንያ ናይሮቢ ውስጥ የሚገኝ አንድ የክልል ቢሮ እና በቡርኪናፋሶ የሚገኘው የ ROWA ጽሕፈት ቤት እስኪዘጋ ድረስ ለተወሰነ ጊዜ የፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ሆኖ እንዲቆይ ተደርጎ ነበር። እ.አ.አ. ከጥር 2005 ጀምሮ ሥራውን የወሰደ አዲስ የአፍሪካ ክልላዊ ዳይሬክተር ተሾመ ። ይህ የጽህፈት ቤት መልሶ ለማደራጀት በአስተዳደር፣ በሕግ፣ በስትራቴጂ፣ በዕቅድ፣ በሰው ኃይል፣ በአባላት የፋይናንስ ተሳትፎና በበጀት ድልድል ረገድ የራሱ አንድምታና መስፈርቶች ነበረው። በአሁኑ ወቅት ዓለምአቀፍ የኅብረት ሥራ ኅብረት-አፍሪካ (አይሲኤ-አፍሪካ)የራሱ የሆነ አመራር ያለው ሲሆን የዋናው ጽ/ቤት መቀመጫ ደግሞ በኬንያ፣ ናይሮቢ ከተማ ነው።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ባወጣው ሪፖርት መሰረት  ሀገራችን ኢትዮጵያ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሚገኙባቸው የአፍሪካ ሀገራት መካከል አንዷ ስትሆን በሀገራችን ወደ 106,876 የሚጠጉ መሰረታዊ ኅብረት ስራ ማህበራት ይገኛሉ። እነዚህ መሰረታዊ ኅብረት ስራ ማህበራት በአጠቃላይ 28,582,005 አባላት ያሏቸው ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 33.9 በመቶው ሴቶች ናቸው። የህብረት ስራ ማህበራቱ አጠቃላይ ካፒታል 50.6 ቢሊዮን ብር አካባቢ (903,571,428.6 ዶላር) አካባቢ ነው። የኅብረት ስራ ማህበራቱ በሀገር ውስጥ ያላቸው የገበያ ድርሻ እስከ 18 በመቶ ሲደርስ የውጭ ንግድ ድርሻቸው ደግሞ 5 በመቶ አካባቢ ነው። የኅብረት ስራ ማህበራት በኢትዮጵያ ለ1,495,391 ዜጎች የስራ ዕድል ፈጥረዋል። በተያያዘም በሀገራችን በአጠቃላይ 22,963 መሰረታዊ  የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት (SACCOS) እና 131 የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ዩኒየኖች አሉ። የእነዚህ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አጠቃላይ የቁጠባ መጠን 59.7 ቢሊዮን (1,066,071,428.6 ዶላር) ሲሆን አጠቃላይ የብድር ተጠቃሚዎች ቁጥር እስከ 1,300,000 አባላት ደርሷል። የቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት ባለፉት 5 ዓመታት በከፍተኛ ደረጃ እያደጉ መጥተዋል። ይህም

የሆነው የአባላቱ የቁጠባ ባህል በመሻሻሉና የቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት ለቁጠባ ትኩረት መስጠታቸው እንዲሁም የአባላት የብድር ፍላጎት እያደገ መምጣቱ፤ የአመራሩ የተቀላጠፈ አሰራር በዕውቀት የተገነባ መሆኑ በቁጠባ ላይ ከፍተኛ ለውጥ እንዲታይ አስችሎታል። ባለፉት አምስት ዓመታት ብቻ የተጠራቀመው ቁጠባ በረዥም ጊዜ ከተጠራቀመው ከ280 በመቶ በላይ ብልጫ ያሳያል።

በሀገራችን ከሚገኙ ፈጣን እድገት እያስመዘገቡ ካሉ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል ግንባር ቀደም ተጠቃሽ የሆነው አዋጭ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃ/የተ/መሰ/የኅ/ሥ/ማህበር ሲሆን ከ132,000 በላይ አባላት ያሉት እና በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ተደማጭነት ያለው የኅብረት ሥራ ማህበር ነው። በተጨማሪም በሀገራችን ከሚገኙ የአይሲኤ አባል እና የACCOSCA ተባባሪ አባል ከሆኑ ሶስት ኅብረት ስራ ማህበራት አንዱ ነው።

## የአዋጭ የናይጄሪያ ተሳትፎ /አዋጭ በናይጄሪያ/

አዋጭ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃ/የተ/መሰ/የኅ/ሥ/ማህበር ከ2008 ዓ.ም. ጀምሮ የዓለም አቀፍ ህብረት ሥራ ህብረት **(International Cooperative Alliance)** አባል ሆኖ በመሳተፍ የተለያዩ ምርጥ ተሞክሮዎችን እና ልምዶችን በማግኘት ላይ ይገኛል። ከዚህም ባሻገር October 15, 2021 በተደረገው የInternational Cooperative Alliance - Africa የአመራር ምርጫ ላይ የህብረት ሥራ ማኅበራችን የሥራ አመራር ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ መስፍን ገ/ሥላሴ ተወዳድረው በቦርድ አባልነት በመመረጥ እያገለገሉ ይገኛል። ይህም ለአዋጭ ትልቅ ዕድልና ስኬትም ጭምር ነው። በተጨማሪም አዋጭ የኅብረት ሥራ ማኅበሩን የምርምርና ግብይት ቡድን መሪና የአለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያ የአይ.ሲ.ኤ አፍሪካ የስርዐተ ጾታ ኮሚቴ አባል (ICA-Africa Gender Equality Committee Member) ሆነው እንዲመረጡ በማድረግ International Cooperative Alliance - Africa ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛል።

አዋጭ በ2016 በጀት አመት የInternational Cooperative Alliance – Africa ባዘጋጀው አህጉራዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት ኮንፍረንስ እና የጾታ እኩልነት ኮሚቴ ስብሰባ ላይ **እ.አ.አ. ከህዳር 03/2016 (November 13, 2023) እስከ ህዳር 05/2016 (November 15, 2023)** በናይጄሪያ፤ አቡጃ ከተማ ተሳትፎ የተካሄደ ሲሆን የአፍሪካ አህጉራዊ የህብረት ስራ ማህበራት ኮንፈረንስ ዋና ዋና ባለድርሻ አካላትን፣ ባለሙያዎችን እና ፖሊሲ አውጭዎችን ከመላው አፍሪካ በማሰባሰብ የኅብረት ስራ ማህበራት በአህጉሪቱ ዘላቂ ልማትን በማስፋፋት ያላቸውን ጉልህ ሚና ለመዳሰስ ያለመ ነበር። ይህ መድረክ የአፍሪካን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ተግዳሮቶችን በኅብረት ሥራ ንቅናቄ ለመፍታት የልምድ ልውውጥ፣ የእውቀት ሽግግር፣ ትብብር እና አዳዲስ መፍትሔዎችን ለማውጣትና ለመፍጠር የተመቻቸ መድረክ ነበር። የዚህ መድረክ ዋነኛ አላማ የነበረው:-

- በአፍሪካ ውስጥ ያሉ የኅብረት ስራ ማህበራት በአፍሪካ ቀጣይነት ያለው

መተዳደሪያ እና ልማት የሚያጎለብቱበትን መንገድ ለመለየት

- የኅብረት ስራ ማህበራት ዘላቂ የሆነ የአፍሪካ ሰላምና ልማትን እንዴት ማራመድ ቻሉ የሚለውን ለመለየት
- በአፍሪካ ዘላቂ ልማትን ለመደገፍ በህብረት ስራ ማህበራት፣ መንግስታት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲዎች መካከል አጋርነት እና ትብብርን ለማዳበር ማስቻል፤

ስለዚህም አዋጭ ጥናታዊ ጽሑፍ በመላክ ጉባኤው ላይ ተሳትፎ ያደረገ ሲሆን በቀረበውም ጥናታዊ ጽሁፍ  ሰለ አዋጭ ግንዛቤ ተፈጥሯል። ጽሁፉ ትኩረት አድርጎ የነበረው በሚከተሉት ሀሳቦች ላይ ነበር፡-

- የአዋጭ ታሪክ እና ምስረታ
- የአዋጭ አገልግሎቶች
- የአዋጭ የአባላቱን ኑሮ ለማሻሻል ያለው ሚና
- የአዋጭ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖ
- የወደፊት አቅጣጫዎችና ምክረ-ሀሳቦች

እንደ 16ኛው የአፍሪካ ክልላዊ ጉባኤ እና ኮንፈረንስ፣ የአይሲኤ - አፍሪካ የሥርዓተ ፆታ እኩልነት ኮሚቴ "በአፍሪካ ውስጥ በኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ ዘላቂነትን በማጎልበት የሴቶች አስተዋፅኦ ላይ ከዋናው የአፍሪካ አህጉራዊ የህብረት ስራ ማህበራት ኮንፈረንስ ጎን ለጎን ዝግጅት አካሂዶ ነበር። በውይይቱ ወቅት አባል ድርጅቶቹ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማስፈን እና ሴቶችን በኅብረት ሥራ ማህበራት ለማብቃት የሚያደርጉትን ጥረት በተመለከተ ወቅታዊ መረጃዎችን አካፍለዋል። ውይይቱ በህብረት ስራ ዘርፍ ውስጥ ዘላቂነት እና ሁሉን አቀፍ ልማትን በማጎልበት የሴቶችን ወሳኝ ሚና አጽንዖት ሰጥቶ በመስራት የስኬት ታሪኮችን እና የሥርዓተ-ፆታ አመለካከቶችን በመላው አፍሪካ የትብብር ተግባራትን በማዋሃድ ስልቶችን አጉልቶ አሳይቷል።

ስለዚህ በዝግጅቱ አዋጭ የሴቶችን እና ወጣቶችን ኑሮ ለማሻሻል እያበረከተ ያለው አስተዋጽኦ ሪፖርት ተደርጓል። በተጨማሪም አዋጭ የሴቶችን አቅም ለማሳደግ እና የፋይናንስ ተሳትፎን ለማሳደግ ቁልፍ ተቋም ሆኖ ማገልገሉ ተጠቅሷል። አዋጭ በኢትዮጵያ ውስጥ ግንባር ቀደም እንደመሆኑ በስርዓተ-ፆታ እኩልነት እና በሴቶች ተጠቃሚነት ላይ ጉልህ ሚና እየተጫወተ ይገኛል። የሥርዓተ ፆታ እኩልነትን ለማስፈንና ሴቶችን በማብቃት ሴቶች ሀብትና ንብረት እንዲያፈሩ በማድረግ፣ የሥራ ዕድል በመፍጠር (ማለትም 59% ሠራተኞቹ ሴቶች መሆናቸው)፣ አመራርና የውሳኔ ሰጪነት ተሳትፏቸውን በማሳደግ (65.63 በመቶ 32 ከፍተኛ እና መካከለኛ ቦታዎች በሴቶች የተያዙ መሆናቸው); ከጠቅላላው አባላት 40 በመቶው ሴቶች ሲሆኑ የተበዳሪውም ቁጥር 37.96 በመቶ መሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበሩ በስርዓተ ጾታ እኩልነት ላይ እያደረገ ስላለው አስተዋጽዖ አመላካች መሆኑን ያሳያል። ለዚህም ማሳያ አንድ ቅርንጫፍ ቢሮ ሙሉ በሙሉ በሴት ሰራተኞች መመራቱ አመላካች ነው። ቀደም ሲል የተቋቋመውን ለማጠናከር አዋጭ የቀጣይ አቅጣጫዎችን በመቀየስ የኅብረት ስራ ማህበረሰቡ ትኩረት ሰጥቶ ሰፊ ርብርብ እንዲያደርግ ማስቻል ይኖርበታል። የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ፣ ለሴቶች በቂ ሥልጠናና ትምህርት መስጠት፣ ተቋሙን ሥርዓተ ጾታን ያማከለ ማድረግ፣ በሥርዓተ-ፆታ ላይ የተከናወኑ

ሥራዎችን ማድመቅ/ማስተዋወቅ፣ ሴቶችን ወደ አመራር ማምጣትና በኅብረት ሥራ ማህበራቱ ልማት የተገኘው ለውጥ በሴቶች ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ይገኙበታል። በተጨማሪም የሴቶችን ተሳትፎ እና ጥቅም በየጊዜው መለካት/ማጥናት አስፈላጊ መሆኑ ተገልጿል።

የጾታ




እኩልነት ኮሚቴ የአፍሪካ አህጉራዊ የህብረት ስራ ማህበራት ኮንፈረንስ (ICA-Gender Equality Committee) Africa $16^{th}$ Regional Assembly and Conference)

**የአዋጭ ቆይታ በኬንያ /አዋጭ በኬንያ/**

**አዋጭ እ.አ.አ. ከህዳር 23/2016 (December $3^{rd}$ 2023) እስከ ህዳር 27/2016 (December $7^{th}$ 2023)** በኬንያ፤ ናይሮቢ ከተማ በተካሄደው Cooperatives for Sustainable Transformation in Africa (COOP-STAR) Workshop ላይ ኢትዮጵያን በመወከል ተሳትፎ ማካሄድ ችሏል። ኮፕ-ስታር (የኅብረት ሥራ ማኅበራት ለአፍሪካ ዘላቂ ትራንስፎርሜሽን) ከ2030 አጀንዳ እና ከዚህም በላይ የአፍሪካ ኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ ያተኮረ የለውጥ ፕሮጀክት ነው። በአፍሪካ ቀጣይነት ያለው እና ለውጥ የሚያመጣ የትብብር ስራ ፈጠራን ለማሳደግ በዓለም አቀፍ ኅብረት ሥራ አሊያንስ እና KU Leuven (የሉቨን - ቤልጂየም ዩኒቨርሲቲ) ጋር በመተባበር የተጀመረ ፕሮጀክት ነው።

የትብብር ስራ ጥናትን፣ ዕውቀትን፣ የኔትወርክ ግንባታን እና ልውውጥን እንደ ጠንካራ መሳሪያ በመጠቀም የኅብረት ሥራ ንቅናቄውን ለማነቃቃት እና የአፍሪካ ዜጎችን የዕለት ተዕለት እና የረዥም ጊዜ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችል ምቹ ሁኔታን ለመገንባት ያለመ ነው። ማህበረሰብን አሳታፊ በመሆኑ፣ CoopStar በፕሮጀክቱ ውስጥ እንዲሳተፉ ሰፊ የባለድርሻ አካላትን (የአካባቢ፣ ሀገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ የትብብር ተዋናዮችን፣ የልማት ኤጀንሲዎችን፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ ምሁራንን፣ የገንዘብ አጋሮችን)

የማሰባሰብ ፍላጎት አለው። የፕሮጀክቱ ዋና ዋና ዓላማዎች፡

- ➢ በአፍሪካ አህጉር ያለውን የኅብረት ስራ ማህበራትን ወቅታዊ እንቅስቃሴ በተሻለ ሁኔታ መረዳት፣
- ➢ በዘላቂ ልማት እና በፍትሃዊ ሽግግር ዓውድ ውስጥ ዋና ተፅእኖ ፈጣሪዎችን መለየት፣
- ➢ በተለያዩ የኅብረት ሥራ ዘርፎች (የፋይናንስ፣ የግብርና፣ የታዳሽ ኃይል፣ ውሃ፣ መኖሪያ ቤት፣ የአቅርቦት ሰንሰለት.....) ዘላቂ ሥራ ፈጣሪነትን ለማጠናከር ቁልፍ ጉዳዮችን፣ እድሎችን እና ተግዳሮቶችን መፍታት ነበር።

ፕሮጀክቱ በአፍሪካ የትብብር ትዕይንት ዋና ዋና አዝማሚያዎች ላይ ወቅታዊ ግንዛቤዎችን ይሰጣል። በስብሰባው ላይ አዋጪ ጉልህ ሚና የተጫወተ ሲሆን ኢትዮጵያ አሁን ያለችበትን የትብብር ደረጃ አስመልክቶ ገለጻ ቀርቧል። በተጨማሪም የመንግስት ቁጥጥር፣ የኅብረት ስራ ማህበራትን በሚመለከት ኃላፊነት ያለው የመንግስት አካል፣ የህግ ማዕቀፍ፣ የኅብረት ስራ ማህበራት ንቅናቄ፣ የፋይናንሺያል ኅብረት ስራ ማህበራት፣ ታሪካዊ አመጣጥ እና አዝማሚያዎች፣ የህብረት ስራ ማህበራት ለዘላቂ ልማት የሚያበረክቱት አስተዋፅዖ፣ ተግዳሮቶች፣ እድሎች እና የኢትዮጵያ የህብረት ስራ ማህበራት ቀጣይ አቅጣጫዎች በገለፃው ላይ ቀርበው ውይይት ተደርጎበታል። ስብሰባውን የኬንያ ብሮድካስቲንግ ድርጅትን ጨምሮ ሌሎች በርካታ ሚዲያዎች ዘግበውታል።

## አለም አቀፍ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በኢትዮጵያ መከበር ያለው አደምታ

**በአቶ መስፍን በቀለ**

አለም አቀፍ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ቀን በኢትዮጵያ መከበር ያለው እድምታ ከፍተኛ ነው። በቅድሚያ ግን የበዓሉ መከበር ያለውን እንድምታ ከማየታችን በፊት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በአለም አቀፍ ደረጃ፣ በአህጉራችን አፍሪካ ብሎም እጅግ በምንወዳት በአገራችን ኢትዮጵያ መቼና እንዴት ተመሰረተ የሚለውን ታሪካዊ አመጣጥን ማየት አስፈላጊ ነው።

### የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በአለም አቀፍ ደረጃ፤

ለመጀመሪያ ጊዜ እ.ኤ.አ በ1850 በጀርመን አገር ተመሰረተ። በዚህ ወቅት ራፋይዘንና ሹልዝ የተባሉ ሁለት ጀርመናውያን በገጠርና በከተማ የሚኖረውን ሕዝብ ከአራጣ አበዳሪዎች አስከፊ ብዝበዛ እንዲላቀቅ እንቅስቃሴ የጀመሩበት ጊዜ ነበር። በወቅቱ ጀርመን ከደረሱበት ችግሮች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

- ❖ ከፍተኛ የስራ አጥነትና የኑሮ ውድነት መስፈን፣
- ❖ ከፍተኛ የሆነ ድርቅ መከሰት፣
- ❖ አርሶ አደሩ፣ ሰራተኛውና የእደ ጥበብ ባለሙያው እጅግ አስከፊ የሆነ የኑሮ ደረጃ ላይ መድረስ፣

ይህን ከላይ የተዘረዘሩትን የችግር መነሻዎች አጋጣሚ በመጠቀም በወቅቱ የገንዘብ ኃይልና ሀብት የነበራቸው ጥቂት ካፒታሊስቶች የአራጣ ብድር መረባቸውን ዘርግተው ሰራተኛውንና

አጠቃላይ ኅብረተሰቡን በመበዝበዛቸው የህብረተሰቡን ኑሮ የበለጠ እየቆረቆዘ እንዲሄድ አደረጉት። በዚህ ሁኔታ በእንግሊዝና በጀርመን በተመሣሣይ ወቅት የተጀመረው በኅብረት ሥራ ማህበር ተደራጅቶ ችግርን የመቅረፍ ሂደት ቀስ በቀስ ወደ ህንድ፣ ፈረንሳይ እና ሌሎች የአውሮፓ አገሮች እንዲሁም በመላው አለም እየታወቀና እየተስፋፋ ሄደ። ዛሬ ላይ የተደራጁት ኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ በመጨመር፣ በአባላት ቁጥር በመጨመርና ከፍተኛ በመሆን እንዲሁም በከፍተኛ ደረጃ የካፒታል እድገት ደርሶ በመላው አለም ላይ ተስፋፍቶ ይገኛል።

በተመሳሳይ በአህጉራችን በአፍሪካ ደረጃም፤ የመጀመሪያው የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የተቋቋመው እ.ኤ.አ በ1955 በጋና ውስጥ ጂሮፓ በምትባል ከተማ ነው። በአፍሪካ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ሊስፋፉና መሰረት ሊጥሉ የቻሉት አህጉራዊ ድርጅት በሆነው በአፍሪካ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን ማለትም አኮስካ/ACCOSCA/ አማካኝነት ነው። ይህንም ድርጅት የ12 አገሮች ብሄራዊ ማህበራት ያቋቋሙት ነው። ኢትዮጵያም ከመስራች አገሮች አንዷ ነች። ጽህፈት ቤቱም በኬንያ ዋና ከተማ ናይሮቢ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት አዋጭ የገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበርም በአገራችን ብቸኛው የአኮስካ/ACCOSCA/ ተባባሪ አባል ነው።

## በአገራችን ኢትዮጵያ ዘመናዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት

በህግ መቋቋም የጀመረው በ1953 ዓ.ም በወጣው ድንጋጌና በ1958 ዓ.ም በወጣው የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ነው። በወቅቱ ተቋቁመው ከነበሩት 154 የተለያዩ ኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ 94ቱ የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ሲሆኑ ቀሪዎቹ 60 የሚሆኑት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ናቸው። በአሁኑ ወቅት በአገራችን ኢትዮጵያ ከ23 ሺህ



በላይ የገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት እንደሚገኙ የኢትዮጵያ ህብረት ሥራ ኮሚሽን መረጃ ያመለክታል።

**አለም አቀፍ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ቀን አከባበር መቼ ተጀ መረ?**

አለም አቀፍ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ቀን አከባበርን በምንመለከትነት ጊዜ ዋና መነሻ ሀሳብ የሆነው የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት እየተስፋፉ ሲመጡ ለአባላት እየሰጡ ያለውን የፋይናንስ አገልግሎቶችን ለሕዝብ ለማስተዋወቅ እና የተገኙ ተሞክሮዎችን ወደ ሌሎች ለማስፋፋት እንዲቻል ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በዓሉን ማክበር ያስፈልጋል በሚል ነው። ከዚህ በመነሳት፡-

❖ **እ.አ.አ. ጥር 17/1927** “Credit Union League of Massachusetts” በሚባል የኅብረት ሥራ ማህበር በአሜሪካን ውስጥ የመጀመሪያው የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ቀን ተከበረ። ቀኑ የተመረጠበት ዋነኛ ምክንያት የቁጠባ አገልግሎት አቀንቃኝ የነበሩት “Benjamin Franklin” የተወለዱበት ቀን በመሆኑ እሳቸውን ለማሰብም ነበር።

❖ **በመቀጠል በ1948 የአሜሪካ** “Credit Union National Association (CUNA)” እና “CUNA Mutual Insurance Society” የተባሉ ተቋማት በአለም አቀፍ ደረጃ በዓሉ መከበር አለበት በሚል መነሻ ሀሳብ በዓሉ ጥቅምት ወር የመጨረሻው ሳምንት ሐሙስ እንዲከበር ተወሰነ። በመሆኑም በዓለም አቀፍ ደረጃ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን እንዲያስተባብርና እንዲደግፍ **እ.አ.አ. በ1971** “World Council of Credit Unions (WCCU) ተመሰረተ። በአሉንም በበላይነት እያስተባበረ ይገኛል።

❖ **October 31, 2022** "የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት ለተጠናከረ የፋይናንስ አቅም" በሚል መሪ ቃል በሃገር አቀፍ ደረጃ ለመጀመሪያ ግዜ በሀገራችን ኢትዮጵያ ተከበረ።



## ጥቂት ስለ ‹‹የእናቱ ልጅ›› መጽሐፍ...

**በአቶ ዮናስ ፍቃዱ እና በአቶ ጌታሁን ታደሰ**

ንብ አበባ ላይ አርፋ ብቻ አትሄድም የማር ምንጭ የሆነውን ኔክታር የተባለውን ብናኝ ቀስማ እንጂ የምትነሳው፡፡ ብዙ ነፍሳት አበባው ላይ ያርፋሉ ግን ጉብ ከማለት ውጪ ምንም ሲፈይዱ አይታዩም፡፡ ንቧ ግን ዘደኛ ናት ምን ከምን ማግኘት እንዳለባት የገባት!

በደራሲና ጋዜጠኛ ደመቀ ከበደ የተፃፈው ‹‹የእናቱ ልጅ›› የተሰኘው መፅሐፍ በጎብረት ሥራው ፈርጥ በአቶ ዘሪሁን ሽለመ እውነተኛ የህይወት ታሪክ ላይ ትኩረት አድርጎ የባለታሪኩን ከ...እስከ ቀልብን በሚስብ፤ ልብን በሚገዛ፤ አእምሮን በሚቆጣጠር፤ ከአንዱ ሀረግ ወደ ቀጣይ ዓረፍተ ነገር ምን አንዳች ነገር ይሆናል በሚያስብል ልብን በሚያንጠለጥል እያጓጓና ቁምነነገር እያስጨበጠ ቀጣዩን ለማወቅ እያስቋመጠ በበሳል የደራሲው የስነፅሑፍ ችሎታ ይዘን ይተማል፡፡ የሀረጉን ጫፍ ይዘው ድምዳሜ ለመስጠት እንዳይሞክሩ ደራሲው እያንዳንዱን የታሪክ ፍሰት የማይገመት አድርጎት ከትቦታል፡፡ ኩልል ብሎ ሳይደፈርስ በጉሮሮ ሰተት ብሎ እንደሚወርድ የምንጭ ውኃ የባለታሪኩን ህይወት አንባቢው ግጥም አድርጎት እንዲያጣጥም በፀሐፊው የሰዋሰው ልህቀት ሲንቆረቆር ይታያል፡፡

መጽሐፉ በሦስት የምዕራፍ አንጓዎች ተሰድሮ ከባለታሪኩ የዕድሜው እሸት እስከ ህይወት ምርትና ግርዱ በቅደም ተከተል ተሰንዷል፡፡ በመጽሐፉ ጅምር ምዕራፍ ላይ የባለታሪኩን የአቶ ዘሪሁን ሽለመ የለጋ ዕድሜ ገጽ እስከ ጎልማስነት የብስለት ዘመን ያለውን ያትታል፡፡ ዘሪሁን ልክ እንደስሙ ዘር ኹን፤ ዘር ያርግኽ ተብሎ ገና በልጅነት የተመረቀ መሆኑን በውስጡ የተሰጠውን መክሊት ሊያበዛ ሲታትርና ሲተጋ፤ ትጋቱም ፍሬ ሲያፈራ መሳጭ በሆነ አቀራረብ ደራሲው በአንባቢያን ላይ የማይጠፋ ስዕል ሲስል ያስቃኘናል፡፡



የተሰጠውን ምናን ወይም መክሊት ሳይቀብር ወደ ወሳኝ የህይወት እርምጃ ሲንደረደር ዛሬ ከራሱ አልፎ ሀገርን ሲያልፍም በአፍሪካ ደረጃ ተፅዕኖ ወደ መፍጠር እያራመደ ያለውን የአዋጭ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበር ምስረታ፣ ታሪክና ዕድገትን በምዕራፍ ሁለት ላይ ሰፊ ሽፋን አግቷል። ከአዋጭ በፊት የተቋቋሙ እጅግ በርከት ያሉ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ነበሩ፤ ቁጥራቸውም ብዙ የሆነ! ከበዙት ውስጥ ነጥሮ የራስን ልዩ ነገር ይዞ መውጣት እጅግ ፈታኝ ነው። ይሁን እንጂ "ስራን መንቀፍ በስራ ነው እንጂ በቃል ብቻ መንቀፍ አይገባም!" እንዲሉ ዘሪሁን አንዳች ልዩ የሚያደርገውን ይዞ መምጣቱን በልበ-ሙሉነት እያሳየ ይህ ምዕራፍ ጭብጥ ይሰጠናል። አዋጭ ከቀደሙት ኅብረት ሥራ ማኅበራት በተለየ ሁኔታ የራሱን ደማቅ አሻራ ከማሳረፍ ረገድ አዲስ አሰራር ዘርግቷል፤ ይኸውም የዘሪሁን ልዩ የመሪነት ጥበብ፣ አሻግሮ ተመልካችነትና ቆራጥነት ውጤት ነው። መጽሐፉ የባለ ታሪኩን የልብ ትርታ ቀርበው ያደመጡ ያህል ስለ አንዱ የትግል ድል ተገርመው ሳይጨርሱ ሌላውን ድገሙኝ እያሰኘ በምዕናብ ኮርቻ አፈናጦ በታሪክ ሰረገላ ያስጋልባል።

በሦስተኛው የምዕራፍ አንጓ ደራሲው የባለታሪኩን በሳል የመሪነት ክህሎት፣ የማህበራዊና የህይወት ፍልስፍናቸውን ሳቢ በሆነ የታሪክ ፍሰት ይተነትነዋል።

ብቻ ግን በእነዚህ ሦስት ምዕራፎች ውስጥ ዘሪሁን ሲባል አዋጭ፤ አዋጭ ሲባል ዘሪሁን የማይለያዩ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ሆነው እናገኛቸዋለን። አዋጭ ደምቆ ሲፃፍ የባለታሪኩ የአቶ ዘሪሁን ሸለመ አበርክቶት የአንበሳውን ድርሻ ይይዛል።

በመጽሐፉ አዋጭ ከድክድክ ጅምር የፈረጠመ ጠንካራ የኅብረት ሥራ ማኅበር እስኪሆን ድረስ ያለውን ዕድገት፣ ፈተና፣ ድል፣ ስኬትና ከፍታ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። አዋጭ ከሀገር አልፎ በአህጉር ደረጃ በኅብረት ሥራው ዘርፍ ትልቅ ተፅዕኖ እያመጣ መሆኑን በጥልቀት ያሳያል።

‹‹የእናቱ ልጅ›› መጽሐፍ መታሰቢያነቱ ለባለታሪኩ እናት ለወ/ሮ አየለች ወርቁ እና ባሎቻቸው ለእናት ሀገራቸው ዘብ በመቆም ላጡ እናቶች፤ በዚህም ልጆቻቸውን ደጅ እንደወንድ ሰርተው ቤት እንደ ሴት ፈግተው እናትና አባት ሆነው ላሳደጉ፣ በብዙ ውጣውረድ ላለፉ እና እያለፉ ላሉ የኢትዮጵያ እናቶች ሁሉ መታወሻ እንዲሆን ተደርጓል።

መጽሐፉ ህዳር 21 ቀን 2016 ዓ.ም በሸራተን



አዲስ ባለታሪኩ፣ የባለታሪኩ ቤተሰቦች እና ወዳጅ ዘመዶች፣ የተለያዩ ደራሲያን እና የጥበብ ሰዎች፣ የፋይናንስ ተቋማት መሪዎች፣ የኅብረት ሥራ ሴክተር አመራሮች፣ ባለሙያዎች እና አባላት እንዲሁም ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው ቤተሰቦች መብቃት እንደሚቻል ትምህርት አዘል መልዕክት ሲተላለፍ የሀገራችን የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበራት በሀገራችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮችን በመፍታት ረገድ ያላቸው አስተዋፅኦ አድናቆት ተችሮታል፡፡

## በአዋጭ ፋውንዴሽን እየተሰሩና ሊሰሩ የታቀዱ ፕሮጀክቶች

**በአቶ አብይ በሻህ**

አዋጭ የገንዘብ ቁጠባና ብድር መሰረታዊ ሕብረት ሥራ ማህበር ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ማኅበራዊ ኃላፊነቶቹን እየተወጣ ሲሆን ከድርጅቱ ዕድገት ጋር ተያይዞ የማኅበረሰቡና የመንግስት ሴክተር መ/ቤቶች ጥያቄ እያደገ በመምጣቱ በሀገር አቀፍም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ካሉ አጋሮቹ ጋር በመሆን በሀገራችን ድህነትን ለመቀነስና ማህበረሰቡን ወደ መካከለኛ ገቢ በማሸጋገር ተጨባጭ አስተዋጽዖ ለማበርከት አዋጭ ፋውንዴሽን በሚል ስያሜ የበጎ አድራጎት ድርጅትን መስርቷል፡፡

አዋጭ ፋውንዴሽን ለትርፍ ያልተቋቋመ፤ መንግስታዊ ያልሆነና፤ ሀገር በቀል ድርጅት ሲሆን፤ ጥር 6 ቀን 2014 ዓ.ም በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን በመዝገብ ቁጥር 6010 ተመዝግቦ በፌደራል ደረጃ በክልሎች ለመሥራት ሕጋዊ ሰውነት አግኝቷል፡፡

በተገኙበት በደማቅ ስነ-ስርዓት ተመርቋል፡፡ በዕለቱም የኢትዮጵያ እናቶች ተዘክረውበታል፤ ለሀገራችን ወጣቶች ልክ እንደ ዘሪሁን በብዙ ችግርና ፈተና ውጣ ውረድ አልፎ ለስኬት

በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ ሁለት ፕሮጀክቶች ቀርጾ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየካ እና አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተሞች እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን ጫንጮ ከተማ ልዩ ልዩ የማኅበረሰብ ልማቶችን እያከናወነ ይገኛል፡፡

በተለይ በጫንጮ ከተማ አዋጭ ፋውንዴሽን በ2400 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የቅድመ መደበኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ከፍቶ ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ የመምህራንና የተማሪዎችን ሙሉ ወጪ ችሎ በሥራ ላይ ይገኛል፡፡

አዋጭ ፋውንዴሽን የአዋጭ /ገ/ቁ/ብ/ኃ/የተ/መሰ/ሕ/ሥ/ማህበርን ማህበራዊ ተሳትፎ በተሟላ መልኩ ለመስጠት እንደመቋቋሙ ራዕዩ፡- “አነስተኛ ገቢ ያላቸው የሕብረተስብ አባላት መሠረታዊ ፍላጎታቸው ተሟልቶ ማየት!” ሲሆን ተልዕኮው ደግሞ “የማህበረሰብ ተሳትፎን በማካተት ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ክፍሎች በትምህርት፤ በጤናና ምግብ፤በማህበራዊ ስነልቦና ድጋፍ፤ በኑሮ ማሻሻያ፤ በአካባቢ ጥበቃና የኃይል አጠቃቀም፤ በድንገተኛና ሰብዓዊ ድጋፎች አማካይነት በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማበርከት ፡፡” ሲሆን እንደ መሰረተው እናት ድርጅት ሰፋ ያለ ነው፡፡ የሥራ ትኩረት አቅጣጫዎቹም ስድስት ሲሆኑ በአሁኑ ጊዜ እየተከናወኑ ያሉትን ሥራዎች በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 1. በትምህርት ዘርፍ

በትምህርት ዘርፉ በአዲስ አበባ ከሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ጋር በመዋዋል ስልሳ ስምንት ልጆች ሁሉን አቀፍ አገልግሎት እንዲያገኙ በቀጥታ ወደ ልጆች አካውንት የሚተላለፍ የገንዘብ ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል፡፡

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ጫንጮ ከተማ ደግሞ በ2016 ዓ.ም 205 (ሁለት መቶ አምስት) ተማሪዎችን በቅድመ መደበኛ እና በመደበኛ ትምህርት ፕሮግራም አገልግሎት እያገኙ ነው፡፡

### 2. የጤና፣ የምግብ፣ የማህበራዊና የስነልቦና ድጋፍ

በዚህ የድጋፍ ዘርፍ በአዲስ አበባና በኦሮሚያ ክልልም የጤና ችግር ያጋጠማቸው ሰዎች እየተደገፉ ሲሆን በተለይ በአዲስ አበባ 100 (አንድ መቶ) ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች በየካ ክፍለ ከተማ በወረዳ 06 የጤና መድን ክፍያ ተደርጎላቸው ዓመቱን ሙሉ የጤና ችግር ሲያጋጥማቸው በነጻ እንዲታከሙ እየተደረገ ነው፡፡ በዚሁ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ደግሞ 37 (ሰላሳ ሰባት) አባላት ያሉት በአዋጭ የገ/ቁ/ብ/ሕ/ሥ/ማ ታዳጊ የእግር ኳስ ቡድን ተደራጅተው ልዩ ልዩ ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡

### 3. የኑሮ ማሻሻያ

ከኑሮ ማሻሻያ ሥራ በተያያዘ በተመሳሳይ መልኩ በአዲስ አበባና በኦሮሚያ ክልል ሰፊ ሥራ እየተሠራ ሲሆን በተለይ በአነስተኛ ኢኮኖሚ ላይ ያሉ እናቶች በራስ አገዝ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ቡድን ተደራጅተው ራሳቸውን በራሳቸው የሚያግዙበትና ከድህነት የሚወጡበት መንገድ እየተመቻቸ ሲሆን በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ በወረዳ 06 ለሦስት የአካል ጉዳተኞች የኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ እና ለ40 (አርባ) ሴቶች የቢዝነስ ስልጠናና የመነሻ ካፒታል ድጋፍ ተደርጓል፡፡

### 4. መጠለያ፣ አካባቢ ጥበቃና የኃይል አጠቃቀም

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ውስጥ የሦስት አቅመ ደካማ እናቶችን ቤት ሙሉ በሙሉ አፍርሶ ደረጃውን የጠበቀ ቤት



ለነዋሪዎቹ በመሥራት አስረክቧል።

በተጨማሪም አዋጭ ፋውንዴሽን በሥሩ የወ/ሮ አየለች ወርቁ መታሰቢያ ፕሮጀክትን የሚተገብር ሲሆን ወ/ሮ አየለች ወርቁ ከብዙ ጀግኖች እናቶች አንዷ ሲሆኑ ልጃቸውን ያለ አባት አሳድገው ለስኬት ያበቁ፤ እነሆ ዛሬ እርሳቸው በሕይወት ባይኖሩም ልጃቸው አቶ ዘሪሁን ሸለመ በአዋጭ ብራንድ የሚጠሩ ሦስት ድርጅቶች አዋጭ /ገ/ቁ/ብ/ኃ/የተ/መሰ/ሕ/ሥ/ማህበር፤ አዋጭ ኢንሹራንስ፤ አዋጭ ፋውንዴሽን እንዲሁም ዘሚ ሪል ስቴት በመመሥረት በመቶ ሺዎች ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን የሕይወት ለውጥ ምክንያት በመሆኑም አዋጭ ፋውንዴሽን የወ/ሮ አየለች ወርቁ መታሰቢያ ፕሮጀክት መስርቶ ልጆቻቸውን ያለ አባት አሳድገው ለስኬት ላበቁ እናቶች እና ለሌሎች እናቶች አርአያ እንዲሆኑ የሚሸልም ድርጅት ነው። በዚህም በ2016 በጀት ዓመት እናቶችን ከመሸለም ረገድ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ወደ ጎዳና የወጡ ሴቶች ሕይወት እጅግ አሰቃቂ በመሆኑ ወደ ማሕበረሰቡ እንዲቀላቀሉና መደበኛ ሕይወት እንዲመሩ ከሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር የማገገሚያ ማዕከል በማሰራት ለምረቃ በዝግጅት ላይ ይገኛል።

### 5. ድንገተኛና ሰብዓዊ ድጋፍ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የካ ክፍለ ከተማ በወረዳ 06 በየዓመት በዓሉ ስጦታ ለ130 (አንድ መቶ ሰላሳ) አረጋውያን ድጋፍ በዓሉን በቤታቸው ደስ ብሏቸው እንዲውሉ የስንዴ ዱቄት፤ የጤፍ ዱቄት፤ ዘይት፤ የገንዘብና ፍላጎታቸውን መሠረት ያደረገ ድጋፍ እየተደረገ ነው።

### 6. የድርጅት አቅም ግንባታ

በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ በወረዳ 06 የፖሊስ ማዕከል ግንባታ የተደረገ ሲሆን በአሁኑ ጊዜም ከፒስ ኤንድ ፕሮዳክቲቭ ድርጅት ጋር በመዋዋል በየካ ክፍለ ከተማ ወንጀልን ለመከላከል የሚያስችል የኮምፒዩተር ስልጠና በስድስት ወር የሚጠናቀቅ ለ60 (ስልሳ) የፖሊስ አባላት ለመስጠት ታቅዶ የመጀመሪያው ዙር 30 (ሰላሳ) ፖሊሶች ለሦስት ወር የሚቆየውን ስልጠና ጀምረዋል።



አዋጭ ፋውንዴሽን ከተመሰረተ ሁለት ዓመት ቢሞላውም የተወሰነ የሰው ኃይል ተሟልቶለት ሥራ ከጀመረ ግን የስድስት ወራት ጊዜ ብቻ ስለሆነ ያለው ከላይ በፕሮግራም ከያዛቸው መደበኛ ሥራዎች ጎን ለጎን በዋናነት የፕሮጀክት ዲዛይን ሥራ፤ ቢሮ የማደራጀት ሥራ፤ የ2014 እና 2015 አፈጻጸምን ፋይናንስ በውጭ ኦዲትር ማሠራት፤ ከመንግስት ሴክተር መ/ቤቶች ጋር ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና ከኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ጋር፤ ከፋይናንስ ቢሮ፤ ት/ት ቢሮ፤ እና ከሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ቢሮዎች ጋር ውል መግባት፤ በመንግስት የሪፖርት ፎርማት መሠረት የሪፖርት ዝግጅት፤ ከልዩ ልዩ ድርጅቶች ጋር በጋራ ለመሥራት የመግባቢያ ሰነዶችና የፕሮጀክት ሥራ (የሜሪ ጆይ ሰፖንሰርሽፕ፤ የወ/ሮ አየለች ወርቁ መታሰቢያ ፕሮጀክት፤ ፒስ ኤንድ ፕሮዳክቲቪቲ) የመሳሰሉትን ትልልቅ ሥራዎች ከአራት በማይበልጡ ፕሮፌሽናል የሰው ኃይል እያከናወነ ይገኛል።

በቀጣይ በእነዚህ ስድስት ዘርፎች አሁን በጀመረባቸው ሁለት ክልሎች ሥራዎቹን አጠናክሮ የሚቀጠል ሲሆን ወደ ፊት በአማራ ክልል እና በደቡብ ክልሎች አዋጭ ቢሮ በከፈተባቸው ቦታዎች ሁሉ ለመሥራት አቅዷል። በጫንጮ ትምህርት ቤት የግንባታ ሥራም ስለሚጀምር እና መደበኛ ፕሮግራሞቹንም በተልዕኮው ልክና ከተመሠረተበት ዓላማ አንጻር ጉልህ ለውጥ ለማምጣት የሀብት ማሰባሰብ ሥራዎችን በስፋት የሚሠራባቸው ዕቅዶቹ ናቸው።



## የአባላት ትምህርት እና ስልጠና ክፍል

**ወ/ሮ ሄለን ይልማ**

አዋጭ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃላፊነቱ የተወሰነ መሰረታዊ የኅብረት ስራ ማህበር የአባላቱን አቅም ለማጎልበት ከሚሰጣቸዉ አገልገሎቶች አንዱ ለአባላቶቹ ትምህርትና ስልጠና ሲሆን ይህንን ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት ኅብረት ስራ ማህበሩ አሁን በደረሰበት የዕድገት ደረጃ መሰረት የራሱ የሆነ የስልጠና ማዕከል ለትራንስፖርት ምቹ በሆነ ቦታ በመሀል ሜክሲኮ በመክፈት አባላቶች በሚመቻቸዉ ጊዜ በተደራጀ መልክ እየሰጠ ያለ ሲሆን በዓለም አቀፍ የህብረት ስራ ማህበራት መርሆዎች ብሎም የሀገራችን የኅብረት ስራ ማህበራት አዋጅን ተከትሎ ተግባራቱን የሚያከናዉነዉ የኅብረት ስራ ማህበራችን ለአባላት፣ለህብረት ሰራ ማህበሩ አመራር አካላትና ለልዩ ልዩ ኮሚቴ አባላትና እና ቅጥር ሰራተኞች ለማኅበራቸዉ ዕድገት ተገቢዉን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ትምህርትና ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል። እንዲሁም አባላቶች የህብረት ስራ ማህበሩን አገልገሎት ሲጠቀሙ ወቅታዊ በሆነ መረጃ መሰረት አድርገዉ ቢሆን የበለጠ ለህብረት ስራ ማህበራቸዉም እንዲሁም እነሱም የተደራጁበትን ተልዕኮ እና ዓላማ ለማሳካት ይረዳቸዋል። በመሆኑም በሰፊዉ አጠናክሮ በመስራት ህብረት ስራ ማህበራትን መሰረት ያደረገ ቤተ-መፅሐፍት፣ የጥናትና የምርምር ተቋም ማዕከል እንዲሆን የወደፊት ግቡም የልህቀት ማዕከል እንዲሆን ማስቻል ነዉ። አሁን እየሰጣቸዉ ያለዉ የአባላት ግንዛቤ ማስጨበጫና ስልጠና በእነዚህ ላይ መሰረት አድርጎ ሲሆን ይኸዉም፡- የአባላት የኅብረት ስራ ማህበር መርህ እና ፅንሰ ሀሳብ፣ እየሰጠ ያለዉን አገልግሎት ማለትም የቁጠባ ፤የብድር ፣አነስተኛ የብድር መድን ዋስትና፣ መተዳደሪያ ደንቦችንና ውስጠ ደንቦችን መመሪያና አዳዲስ የተጀመሩ ነገሮችን፣ በየጊዜዉ የተሻሻሉ መተዳደሪያ ደንቦችን እና የአባላትን መብትና ግዴታዎችን



በተመለከተ እንዲሁም ቆጥበዉ ብድር ለመበደር የተዘጋጁ አባላትን ስለ ብድር አስተዳደርና አጠቃቀምን ተበዳሪ አባላት ዕዉቀት ኖሯቸዉ በወሰዱት የብድር ገንዘብ እንዴት ዉጤታማ መሆን እንደሚችሉ ገንዘቡን በማስተዳደር ዉጤታማ እንዲሆኑ የማስቻል ዘዴን/ክህሎትን፣ የስራ ፈጠራ እንዲሁም ንግዳቸዉን እንዲያሳድጉ የሚያስችል የሙያ ስልጠናዎችንና የማማከር አገልገሎቶችን የመሳሰሉትን በሰፊዉ የሚሰጥ ሲሆን የአባላት በስልጠና እና ግንዛቤ ማስጨበጫዎች ላይ መሳተፋቸዉ ለህብረት ስራ ማህበራቸዉ ንቁ የሆኑ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ያደርጓቸዋል፤ በአገልገሎቱም ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን እዉቀት በመዉሰዳቸዉ በኑሮአቸዉ ላይ ከፍተኛ ለዉጥ እንዲያመጡ ያስችላል። በመሆኑም የኅብረት ስራ ማኅበሩ የስልጠና ማዕከል በየቀኑ ስልጠና ለመስጠት ተዘጋጅቶ ይህንን የስራ ከፍል ከፍቶ እየሰራ ያለ ሲሆን በተለይም አዳዲስ ወደ ህብረት ስራ ማህበሩ የሚቀላቀሉ አባላቶችን እና ለራሳቸዉ ተጨማሪ ገቢ ፈጥረዉ ራሳቸዉንም ይሁን ቤተሳበቻዉን እንዲሁም ለሌሎችም የስራ እድል መፍጠር ለሚፈልጉና ለሚያስቡ አባላቶቻችን ቅድሚያ ሰጥተን አገልገሎቱን እንዲያገኙ የምናደርግ በመሆኑ አባላት መጥተዉ ይህንን አገልገሎት መጠቀም ቅድሚያ የሚሰጠዉ ጉዳይ ሲሆን እንዲሁም ያለምንም ክፍያ የማህበራቸዉን ሀብት/ጥቅም በጋራ መጠቀም ሲሆን አባላቶች በማህበራቸዉም ዉስጥ ይሁን በተለያዩ ቦታዎች ለዉሳኔ ለመሳተፍ እንዲችሉ የሚረዳ በመሆኑ ኅብረት ስራ ማህበሩ በሰፊዉ ለመስራት በቂ አቅም እና ተነሳሽነት ስላለዉ አባላት መጥተዉ መሳተፍ እንዲችሉ የአባላት መረጃ የማግኘት መብትም ግዴታም ሲሆን በኅብረት ስራ ማህበሩ ዉስጥ ያሉ ባለሙያዎች አባለቱን የማገልገል ግዴታቸዉ በመሆኑ ለሁሉም አባላት ጥሪ የሚያስተላልፍ ይሆናል ።

## ምርጡ ኢትዮጵያዊ

በለኮሰው ቀንዲል በብርሃን ፋና
ከሀገር ጥጉ ሚዛን እስከ አዲሱ ሆሳዕና
ከቅርቡ ኦሮሚያ አማራ ሲዳማ
በአዲስ አበባና በአርባ ምንጭ ከተማ
ትንታግ ለውጥ ይዞ ለህዝቡ የተነሳ
እንዳይሆን ሊያደርገው የህዝቡን አበሳ
ተሻግሮ ከሀገሩ ዘልቆ ወደ ኬንያ
ያለ የአፍሪካንም ችግር ደግሞ ልያ
ቦትስዋና እንዴት ናት ደግሞስ ሞሪሽየስ
በስውር ዓይን አይቶ ለውጥ የሚቀይስ
ወደ መካከሏ ምስራቂቷ ዱባይ
ደግሞ የተሻለ ልምድ ካለ በልቡ ሊያይ
ስለ ኔዘርላንዱ በሌላ ልመለስ
አሁን ከዱባዩ እ ቤልጂየም ሲደርስ
ደግሞ ከቤልጂየም USAን ሲያዳርስ
ስለናፍቆቱ ነው ጥቂት የምዳስስ
"እ" ብሎ የወለደው ሀሳብ ቃል ተግባሩ
አዋጭ በየዕለቱ ነው የስስት ፍቅሩ
እኔም ይህን ጎበዝ በስድስት ስንኝ
እንዲህ ስል ከተብኩኝ፡-
"ቁጣው ፍቅር አዘል ፍቅሩ ኮስታራ
ልግምን የማይወድ ሰርቶ የሚያሰራ
የኅብራት ስራው ፈርጥ የትጋት አውራ
ቀድሞ ተመልካቹ አይቶ የሚመራ
ትጉህና ገስጋሹ ነገውን ያለመ
ምርጡ ኢትዮጵያዊ ዘሪሁን ሸለመ"

ገጣሚ፡ ጌታሁን ታደሰ

## ዘር ሆኗል ዘሪሁን

ዘር ሆኗል ዘሪሁን ተሸልሟል ለሀገር
ስጦታ ተደርጎ ለዚህች ሽልም ምድር
ወርቅ ሀገር ወርቅ አላት ፈጣሪ ያደላት
ከፍ አድርገው ሚያደምቋት ልክ እንደ ጉልላት
ናፍቂ አንቺ አፍሪካ ታገሺኝ አንቺ ዓለም
የኢትዮጵያ ከፍታ ይታያል ዘዳግም
ተራዋ ስለሆነ ልትቆም በዕጣ ክፍሏ
ዕወቁት ተረዱት ቅርብ ነው ማየሏ
"ይቻላል" ልምዷ ነው ችላለች በአዋጭ
ለአፍሪካውያንም ትሆናለች ለዋጭ

ገጣሚ፡ ጌታሁን ታደሰ

## ሀ ብዬ ቁጠባን

ሀ ብዬ ቁጠባን በትንሿ ሳጥን

ትንሽ ነው ብዙ ነው ምኑንም ሳልመጥን

ብቻ ሳንቲሞቼን በትንሿ ባንኬ

ኪል...ኪል...እያረኩ ሳስገባ በልኬ

ጥቅሙ ባይገባኝም

እቅድና አላማ ራዕይ ባይኖረኝም

ዝም ብዬ አስገባለሁ

ትንሿንም ባንኬን ሳንቲም እሞላለሁ።

ዛሬ ላይ አድጌ አላማው ሲገባኝ

ራዕይ ሰንቄ ነገን እያቀድኩኝ

ቁጠባ እየቆጠብኩ በሁለት እግሬ ቆምኩኝ

በእቅድ ሰርቼ ቤተሰብ መስርቼ

መኖርን እንድችል ሁሉን አብቃቅቼ

ህይወቴ እንዲቃና እንዲሰምር አላማዬ

ቁጠባዬ ዋስትና ነው ህልውና ለነገዬ

የወደፊት እቅድ አላማዬን ማሳኪያዬ።

ብኩንነት ስልጣኔ ይመስል የነበረ

ቁጠባ 'ቋጣሪ' ያስብል የነበረ

መቆጠብ መሰልጠን በሚል ተቀየረ

'ለለውጥ እንቆጥብ'ን በስራ አስተማረ።

ካለን ላይ ቀንሰን ዛሬን እንቆጥብ

ዋስትና እንዲሆነን ለነገም እናስብ

ለዚህ መልካም ሀሳብ ሁልጊዜ ተመራጩ

ልክ እንደስሙ ነው መከታ ነው አዋጩ።

**ገጣሚ ቤቲ ፅጌ**

## ቆጥብ

ቆጥብ በል ቆጠብ

ከወጪ ከሰበብ

ጣር ልትኖር በቀመር

ጀምር ዓላማ-መር

አስቀምጥ ዛሬ ታግለህ

ነግ ዘና ትላለህ

አትፍራ መበደር

ፍፁም አትግደርደር

የዛሬ የብር ዋጋ

እንክት ሲል በአንጓ

ዛሬ የበዛብህ

ነገ ሲቀልብህ

እመነኝ ትላለህ ልውሰድ ጨማምሬ

በጣም ረድቶኛል ያለፈው ብድሬ

መልካም ምክር ነው ሃብት ገንዘብ አርገው ዛሬ

ከመባከን ሕይወት ና ሁን ባለ ፍሬ

አዋጬች ነን እኛ በህብረት ያበርን

**ግዳችን ገዳችን** ሰው ነው ገንዘባችን

**ገጣሚ፡ ጌታሁን ታደሰ**

## በዓለም የኅብረት ሥራ ታሪክ አሰደናቂ እውነታዎች

በወ/ሮ ሩት ዳምጣቸው

- ✓ በአለማችን 1 ቢሊየን የሚጠጉ ሰዎች የኅብረት ሥራ ማህበር አባላት ሲሆኑ 44 በመቶ የሚሆሁት በእስያ የሚገኙ አባላት ናቸው። በተጨማሪም ከ 3 አሜሪካዊ ዜጋ አንዱ የኅብረት ሥራ ማህበር አባል ነው።

- ✓ ሮበርት ኦወን (1771-1858) የዘመናዊው የኅብረት ሥራ ማህበር ንቅናቄ አባት ሲሆን የዌልስ ተወላጅ፣ የማህበራዊ ለውጥ አራማጅ፣ የጨርቃጨርቅ አምራች እና በጎ አድራጊ ነበር።

- ✓ በብሪታንያ ከወተት አምራች ኅብረት ሥራ ማህበራት ከሚገኝ ወተት በየቀኑ ከ2.3 ሚሊዮን ሊትር በላይ ወተት ይሸጣል

- ✓ በብሪታንያ ካሉ የኅብረት ስራ ማህበራት ከሚገኝ ምርት በዓመት 20 ሚሊዮን ጠርሙስ ወይን ይሸጣል። ቸርስ!

- ✓ በስዊድን ሁሉም የደን ኢንዱስትሪ የሚካሄደው በኅብረት ሥራ ማህበራት ነው።

- ✓ በጃፓን ቤተ መንግሥት ውስጥ የሠራተኞች የኅብረት ሥራ ማህበር አለ.

- ✓ በሰሜናዊ ጣሊያን ኢሞላ ከተማ ከግማሽ በላይ ገቢ የሚገኘው በሕብረት ሥራ ማህበራት ነው።

- ✓ የኅብረት ሥራ ማህበራት በአውሮፓ ውስጥ ለ1.8 ሚሊዮን ሰዎች የስራ እድል መፍጠር ችሏል።

- ✓ የአሜሪካ ገበሬዎች ግዙፉ የኤሌትሪክ ሃይል ማመንጫዎች የኤሌትሪክ ሃይል እንደማይሰጡዋቸው ሲያውቁ የራሳቸውን የገጠር ኤሌክትሪክ ህብረት ስራ ማህበራት አቋቁመዋል።

- ✓ ከሞላ ጎደል ሁሉም የካናዳ ስንዴ የሚሸጠው በግብርና ህብረት ስራ ማህበራት ነው።

- ✓ የብሪታንያ የቀብር አስፈጻሚ የኅብረት ሥራ ማህበር በየዓመቱ ከ170,000 በላይ የቀብር ሥነ ሥርዓቶችን ያደርጋል።

- ✓ ከብሪታንያ በኋላ በዓለም ላይ ትልቁ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበር በጃፓን ውስጥ ይገኛል።

- ✓ ከብሪታንያ በኋላ በዓለም ላይ ትልቁ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበር በጃፓን ውስጥ ይገኛል።

- ✓ የአውሮፓ ትልቁ ባንክ ክሬዲት አግሪኮል የሚባል ሲሆን የፈረንሳይ ገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማህበር ነው።

**እነዚህ አስቂኝ እውነታዎች እ.አ.አ. በ1995 ለሮቾዴል 150ኛ አመታዊ በዓል ከተዘጋጁት ከCo-op Union ፣ UK 150 አስቂኝ እውነታዎች መካከል የተቀናበሩ ናቸው። (ምንጭ፡ iica@coop.org)**

"Cooperatives Build a Better World", 2022 International day of cooperatives – ILO

"Cooperatives for building a people-centred and environmentally just recovery", 2021 International day of cooperatives – ILO

"COOPS 4 CLIMATE ACTIONS".

International day of cooperatives 2020 – the United Nations

"Sustainable consumption and production",

International day of cooperatives 2018 – the United Nations

"COOPS 4 DECENT WORKS".

International day of cooperatives 2019 – the United Nations

**Cooperatives coats**

"The more generous we are, the more joyous we become. The more cooperatives we are, the more valuable we become. The more enthusiastic we are, the more productive we become. The more serving we are, the more prosperous we become".

William Arthur Ward

We are stronger as a group than an individual. Think in a cooperative and communal way, set up local food hubs and create growing communities.

Arthur Potts Dawson

The cultivation of sensibility on purely personal lines may, in fact, be the very worst training for a world where only the corporate and the cooperative will matter.

John Grierson

Among the qualities most needed among those who aspire to true leadership in the fostering of peace and goodwill among the nations and in overcoming racial and religious antagonism is the cooperative spirit and objective.

John Mott

# ከፎቶ ማህደር













AWACH
አዋጭ



**ወ/ሮ ሰላማዊት ሀይሌ**

**በአቶ ዳዊት ምስራቅ**

ትውልድና እድገቷ አዲስ አበባ ተ/ሀይማኖት አካባቢ ነው። የተለያዩ አልባሳትና እቃዎች በየአይነቱ ከሚሸጡበት አካባቢ ነው ተወልዳ ያደገቸው። ባህር በሆነው የንግድ እንቅስቃሴ መንደር ውስጥ ተወልዳ እንደማደጓ ለንግድ ያላት ፍላጎቷን ሳይጨምረው አልቀረም። ይህ ፍላጎቷ ከአዲስ አበባ ተከትሎ ቢሾፍቱ ድረስ ዘልቋል በአፍላ ወጣትነት ዕድሜ ላይ ልጅ ብትወልድም መውለዱ የልጅነት ህልሟን ከማሳካት አልገደባትም። ተፈጥሮ በሰጠቻት ቅልጥፍና ተጠቅማ በቢሾፍቱ ከተማ ውስጥ ሦስት የአልባሳት ሱቆችን መክፈት ችላለች። በህብረትሥራ ማህበራችን ባገኘችው የብድር ድጋፍ የተንጣለለ ቪላ ቤት ለመሥራት በቅታለች፡ ፡ የዛሬዋ የ‹‹ስኬት ማህደራችን›› እንግዳ ወ/ሮ ሰላማዊትሀይሌ ጋር ያደረግነው ቆይታ እነሆ መልካም ንባብ።

ወ/ሮ ሰላማዊት ሀይሌ እባላለሁ የምኖረው ቢሾፍቱ ከተማ ወይም ደብረ ዘይት ነው ባለ ትዳር እና የአራት ልጆች እናት ስሆን አንድ ሴት ልጅ እና ሦስት ወንዶች አሉኝ ወደ አዋጭ ከመግባቴ በፊት እነግድ ነበር። የምሰራበት ሱቅ ነበረኝ። በሰዓቱ የአዋጭ ሰራተኞች ወደ አዋጭ አባልነት እንድገባ ሱቅ ድረስ እየመጡ ይጠይቁኝ ነበር። ነገር ግን ብዙም ትኩረት አልሰጠሁትም ነበር። በአጋጣሚ አዋጭ አባል ሆኖ በደንብ የተጠቀመ አንድ ወዳጄ ያለውን ሁሉ ነገር ሲያስረዳኝ ቀጥታ ወደ አዋጭ ቢሾፍቱ

ቅርንጫፍ በመሄድ በአባልነት ተመዘገብኩኝ። አሁን አዋጭ አባል ከሆንኩኝ ሦስት አመት ሆኖኛል። አዋጭ አባል ያልሆኑኩበት ጊዜ ሳስበው አሁን ላይ ይቆጨኛል። ምን አለ ቀድሜ አባል በሆንኩ ኖሮ ብዙ ነገሮችን መቀየር እችል ነበር። ወደ አዋጭ ከመግባቴ በፊት ጫማ እና ቢጃማ መሸጫ ሱቆች ነበሩኝ አዋጭ አባል ከሆንኩኝ በኋላ ከሱቆቹ ከሚገኘው ገቢ ላይ አዋጭ መቆጠብ ጀመርኩኝ። ከዚህ ውጪ ከነጋዴዎች ጋር በጋራ የምንጥለው እቁብ ነበረ። እሱ ደርሶኝ መሬት መግዛት ቻልኩኝ። የቤቱንም መሠረት ካወጣው በኋላ መሥራት ከበደኝ እንዳሰብኩት ሳይሆን ብሩም አለቀ። ለንግድ እንቀሳቀስበት የነበረውን ገንዘብ ወደ ቤቱ እንዳላውለው የንግድ እንቅስቃሴውን ይቀንስብኛል። በዚህ ሰዓት ለምን ከአዋጭ አልበደርም? የሚል ሃሰብ መጣልኝ። አዋጭ ቅርንጫፍ በመሄድ አማከርኳቸው። መብትሽ ነው በቆጠብሽው መሰረት የፈለግሽውን ያህል መበደር ትችያለሽ አሉኝ። እኔም የመጀመሪያ ዙር ብድር 400,000,00 (አራት መቶ ሺህ) ብር በመውሰድ ቤቱን ገንብቼ ጨረስኩኝ። የፊኒሺንግ ስራ ብቻ ይቀርብኝ ሰለነበር ሁለተኛ ዙር ብድር በመውሰድ ቤቱን ሙሉ በሙሉ ማጠናቀቅ ቻልኩኝ። አሁን ለእኔ ይሄ መነሻዬ ነው። ከዚህ በተሻለ ከአዋጭ ጋር ለመሥራት አስባለሁ። ቀድሜ አዋጭ ከጎኔ መሆኑን ባገናዝብ ኖሮ አሁን ላይ እንደሰራሁት ዓይነት ቤት ሳይሆን G+3 የሆነ ቤት መሥራት እችል ነበር። አንዳንዴ ከያዘን ድንዛዜ የምንነቃበት ጊዜ አለ እና ዛሬ ነቅቻለሁ። ከዚህ በኃላ እሰራለሁ። የወሰድኩትን ገንዘብ ለመመለስ የቀረኝ 12 ወር ብቻ ነው። በአጭር ጊዜ በመዝጋት የተለየ ሥራ ለመሥራት ዝግጁ

ነኝ። ከዚህ በፊት ብድር በመፍራቴ ባለኝ ነገር ብቻ ነበር መኖር የምፈልገው። ያለችኝን ነገር አብቃቅቼ ብድር እንዲኖርብኝ አልፈልግም ነበር። መኖር የሚመስለኝ ከብድር ውጪ ነበር። ግን ተበድሮ መሥራት እንደሚያሳድግ አሁን ነው የገባኝ። ተበድረክ ካልሰራክ ከፍ ማለት አትችልም። ስትበደር እንድትጠነክር እንድትበረታታ ያደርግሃል። እኔ አሁን ብድር በመበደሬ ብድሩን ከፍዬ ቀጣይ የምሰራውን ነው የማቅደው ብድርን በሁለት መልኩ ነው የምመለከተው፡ አንደኛው ብድር ሳታቅድ ወስደህ ገንዘቡን ያለ አግባብ የምትዘራው ከሆነ በዚህ መልኩ ብድር ባትወስድ ይመከራል።

እኔ ግን ለመበደር ሳስብ እቅድ ይኖረኛል። ገንዘቡን በምን አይነት መልኩ መጠቀም እንዳለብኝ አውቃለሁ። በአግባቡ በመጠቀም እቅዴን አሳካለሁ። በእቅድ ለሚሰራ ሰው ብድር ጠቃሚ ነው ብዬ እመክራለሁ። በተለይ ከአዋጭ መበደር ከቤተሰብ እንደ መበደር ነው። ሠራተኞቹም በጣም ይንከባከቡናል። ልክ እንደ ቤታችን እንድንናፍቀው አድርገውናል። በአሰራራቸው፣ ባላቸው መልካምነትና ቅንነት ገዝተውናል። በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የምታነሳቸውን ጥያቄዎች ሳይቀር በአካል መምጣት እንኳን ባትችል ያለህበት ድረስ በመምጣት ሃሳብ ይሰጡሃል። በዚህ መልኩ ብትሰራው ውጤታማ ትሆናለህ ብለው መንገዱን ያሳዩሃል። የእነሱ መልካምነት ለእኛ እድገት ይጠቅመናል። እኛም በአገልግሎታቸው ተደስተን አባለት ወደ ማህበራችን እንዲመጡ እየጋበዝን ነው። ባለቤቴም የአዋጭ አባል ነው። ጓደኞቼም በአጠቃላይ 20 የሚጠጉ ሰዎች ወደ አባልነት እንዲመጡ አድርጌአለሁ። ባገኘሁት ሁሉ አጋጣሚ ስለ አዋጭ እናገራለሁ። ቡዙዎችም ገብተው ተጠቃሚ ሆነዋል። አዋጭ እንደ ስሙ አዋጭ ነው። ለምሳሌ ልጅ ከመውለዴ በፊት እንደ ልጄ ያሳደግኳትን ልጄን ጨምሮ አራቱም ልጆቼ የህፃናት የቁጠባ ሒሳብ ደብተር አውጥቼ ለሁለት አመት ያህል እየቆጠቡ ይገኛሉ። አዋጭ ፍቅር ነው። በአጠቃላይ የቢሾፍቱ አዋጭ ቅርንጫፍ ሰራተኞችን ላመሰግናቸው እወዳለሁ።



## የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በሀገራችን ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ችግሮች ላይ ያላቸው ሚና

በአቶ ብርሃኑ ዱፌራ

የኅብረት ሥራ ማህበራት ውልደታቸው የአባሎቻቸውን ኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ ችግሮችን ለመፍታት አስቻይ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ነው፡፡ ኢ-ፍትሐዊነት እና አድሎአዊ አሰራር በኅብረት ሥራ ማህበራት ፍልስፍና ውስጥ በጽኑ የሚወገዝ አካሄድ ነው፡፡ በዓለማችን የኢንዱስትሪ አብዮትን ተከትሎ በተለይም በአውሮፓ ተከስቶ የነበረው የተሻለ ትምህርት፣ ዕውቀት እና ገንዘብ ያላቸው ሕዝቦች የተሻለ የሥራ እድል አግኝቶ ሻል ያለ ኑሮ ሲኖር ሌሎች ይህንን ማሟላት የማይችሉ በሰቆቃ እና በከፍተኛ ችግር መኖር የግድ ሆኖባቸው ነበር፡፡ በተጨማሪ በተፈጥሮ ምክንያት በተከሰቱ ድርቅ እና መሰል ችግሮች የተነሳ አቅም የሌላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ችግሮቹን ለመቋቋም ባለመቻላቸው ምክንያት ለከፍተኛ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ ሲዳረጉ ቆይተዋል፡፡

በወቅቱ የነበሩ ምሁራን ይህንን ችግር ለመቀልበስ የሚያስችሉ መላምቶችን ሲያሰላስሉ ቆይተው ከብዙ ሙከራዎች በኂላ ሰዎች በሌሎች ላይ ጥገኛ መሆን ሳያስፈልጋቸው ራሳቸውን በራሳቸው የሚረዱበት ፍልስፍና በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ አካባቢ ዕውን ማድረግ ቻሉ፡፡ ይህ ለዓለማችን ተስፋ የሆነ ፍልስፍና "የኅብረት ሥራ ማህበር" ተብሎ ተጠራ፡፡

በአሁኑ ወቅት በዓለማችን ባደጉም፣ በማደግ ላይ ያሉም ሆነ ባላደጉ ሀገሮች ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሕብረተሰቡን የኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ችግሮችን በመቅረፍ ከዚህም አልፎ ለሀገራዊ ዕድገት የጎላ አስተዋጽዖ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁት ዘርፈ ብዙ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሆኖ ውጤታማ የሚሆኑባቸው የሥራ ዘርፎች እንደየሀገራቱ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ የፖለቲካ ፍልስፍና፣ የስነ-ምህዳርና ሃብት ሊለያይ ይችላል፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ የኅብረት ሥራ ማህበራትን አደራጅታ የሕብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ችግሮች እንዲቀርፉ ማድረግ ከጀመረች ስድስት-አስርት ዓመታትን አስቆጥራለች፡፡ በቀደምትነት ከተቋቋሙ የኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዋነኞቹ ነበሩ፡፡ አደረጃጀቱ እና የተሰጠው ትኩረት እንደየስርዓቱ የተለያየ በመሆኑ ሀገራችን በሕብረት ሥራ ማህበራት ዘርፍ መድረስ

ከሚገባት አንጻር ሲታይ በሚፈለገው ልክና መጠን ግቡን መምታት አልቻለም፡፡

በንጉሱ ዘመን የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚያደራጀው ብሔራዊ ባንክ ሲሆን አደረጃጀቱ በትላልቅ ከተሞች ተቋምን መሠረት ያደረገ በመሆኑ ከተደራሽነት አንጻር ሲታይ እጅግ አነስተኛ ነበር፡፡ ሆኖም ተቋሙን ለማጠናከር ሲባል ተደራጅተው የነበሩ መሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት Ethiopian thrift and cooperative association የሚባል ተቋም ተመስርቶ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ጀምሮ ነበር፡፡

ቀጥሎ የመጣው ሶሻሊዝም ስርዓት ሲሆን የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚያደራጀው ብሔራዊ ባንክ ሲሆን በንጉሱ ዘመን ተደራጅተው የነበሩ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት እና ያቋቋሙት apex ፈርሶ እንደገና እንደአዲስ የማደራጀት ተግባር ተከናውኗል፡፡ በዚህ ወቅትም ቢሆን የተቋቋሙት የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በንጉሱ ወቅት እንደነበረው በትላልቅ ከተሞች ብቻ የታጠሩ ነበሩ፡፡ ሆኖም በሁለቱም ስርዓቶች የነበሩ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ከሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ሲነጻጸር በአንጻራዊነት በአባላት የሚመሩ፣ የአባላትን ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ችግሮችን የፈቱ በመሆናቸው ቀጣይነታቸው የተሻለ እንደነበረ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ባለፉት 20 ዓመታት መንግስት ለዘርፉ በሰጠው ትኩረት የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት በከተማ ብቻ ተወስኖ የነበረው ወደ ገጠር ተስፋፍቶ በአፍሪካ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ያሉባት ሀገር ሆናለች፡፡ በሀገራችን የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በገጠርና ከተማ ከመደበኛ ባንኮች ተጠቃሚ ያልሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የፋይናንስ ንቃተ-ሂሊና በማሳደግ ከፍተኛ አስተዋጽዖ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡

በተጨማሪም የሕብረተሰቡን ባህልና አኗኗር መሠረት ያደረጉ የፋይናንስ አገልግሎቶችን በማስፋፋት ቁጠባን በስፋት በማሰባሰብ ሕብረተሰቡን በቅርበት በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡ የአባሎቻቸውን የብድር ፍላጎት መሠረት በማድረግ ብድር በተመጣጣኝ ዋጋ እና ባልተወሳሰበ መልኩ በማቅረብ የዜጎች ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ችግሮችን በመቅረፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ በከተሞች ዜጎች ተበድረው በትራንስፖርት፣ በጥቃቅን ንግድ፣ በቤቶች ግንባታ እንዲሰማሩ በማመቻቸት፤ በገጠር በግብርና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ በሌሎች ተጓዳኝ የገቢ ማስገኛ ተግባራት ላይ በመሰማራት በተለይም ሴቶች እና ወጣቶችን በከፍተኛ ደረጃ ውጤታማ እንዲሆኑ በማድረግ ለሀገራችን ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ዕድገት የበኩላቸውን አስተዋጽዖ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡

መንግስት እነዚህን ጅምር ጥረቶችን ለማጠናከር በዘርፉ ላይ የሚታዩ የዕውቀት፣ ክህሎት እና

የተደራሽነት ችግሮችን ለመቅረፍ ሀገራዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሪፎርም ዘርግቶ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ሪፎርም በዋናነት ትኩረት የሚያደርገው የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀትን ፈትሾ ማስተካከል፤ አመራራቸውን፣ አሰራራቸውን እና የአገልግሎት አሰጣጣቸውን ቀልጠፋና ዘመናዊ እንዲሆን ማድረግ፣ የፋይናንስ እጥረት የሚቀረፍበትን አቅጣጫ ማስቀመጥ፣ መተግበር እና የቁጥጥር ስርዓታቸው የተጠናከረ እንዲሆን ማስቻል የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ እነዚህ ችግሮች ከተቀረፉ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በአህጉራችን አፍሪካ ተወዳዳሪ ከመሆን ባለፈ ለሀገራችን የፋይናንስ ተደራሽነት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ማበርከት የሚችሉ ተቋማት ይሆናሉ፡፡